3) በኢትዮጵያ የተለያዩ ሃይማኖቶችና የእምነት ክፍሎች አድነት መልካም የሚሆነው እንዴት ነው?

4) አደገኛ የሚሆነውስ?

ረ. በዘፍጥረት ጥናትህ እስከዚህ ድረስ የተማርሃቸው አንዳንድ አበይት ትምህርቶች ምንድናቸው?

5. ጸሎት።

ትምህርት ስድስት

ዘፍጥረት 12-15

የመጀመሪያ ቀን፡- ዘፍ. 12፡1-9

ባለፈው ሳምንት ከአብራም ቤተሰብ ጋር ተዋውቀናል። ሙሴ፥ የአብራም አባት ታራ እንዴት ዑርን ለቅቆ ወደሞተበት ወደ ካራን እንደ ሄደ ተርኮልናል። ዘፍጥረት በአብርሃም ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ፥ ከ12-25 ድረስ ሕይወቱን ይተርክልናል።

1ኛ ጥያቄ፤- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብርሃም እንደዚህ አስፈላጊ ሰው የሆነው ለምን ይመስልሃል?

በዓለም ታሪክ ውስጥ የአብርሃምን ያህል አስፈላጊነት ያላቸው ሰዎች ጥቂት ናቸው። የአብርሃምን ታሪክና እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን መረዳታችን፥ ለመጽሐፍ ቅዱስና ለዓለም የወደፊት ዕጣ ለሚኖረን ግንዛቤ መሠረት ነው።

ሦስት አበይት ሃይማኖቶች፥ አብርሃምን የእምነት አባታቸው አድርገው ይቀበላሉ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ለመመሥረት ቃል ኪዳን የገባው ከአብርሃም ጋር ስለ ነበር፥ አይሁዶች አብርሃምን የመጀመሪያው አይሁድ አድርገው ይመለከታሉ። ሁለተኛ፥ ክርስቲያኖች አብርሃምን ለሚያምኑት ሁሉ የእምነት አባት አድርገው ይመለከቱታል። ሰዎች አብርሃም የነበረው ዓይነት እምነት ከሌላቸው፥ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ሊደባለቁ አይችሉም። ሦስተኛ፥ ሙስሊሞች አብርሃምን እንደ አባታቸው አድርገው በመመልከት፥ እግዚአብሔር የእስማኤልን ትውልዶች እንደሚባርክ ያምናሉ።

ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን፥ ሁለቱም በአብርሃም ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋሉ። አብርሃም የተመረጠው የአይሁድ ሕዝብ አባት ነበር። እንዲሁም ደግሞ እንዴት እግዚአብሔርን በእምነትና በመታዘዝ ሕይወት ደስ ማሰኘት እንደሚቻል የሚያሳይ ቁልፍ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን ገብቷል። ይህም ሌሎቹ ቃል ኪዳኖች ሁሉ፥ ማለትም የሙሴ፥ የዳዊት፥ እና አዲሱ ኪዳን የተመሠረቱበት ኪዳን ነው።

እንዲሁም አብርሃም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ጳውሎስ አብርሃም ሥጋዊ አይሁዶች የሆኑት የእስራኤላውያን ብቻ ሳይሆን፥ የመነፈሳዊ አይሁዶችም አባት እንደሆነ አመልክቷል። ስለሆነም በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ የአብርሃም ልጆችና እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የገባው ቃል ኪዳን ወራሾች ናቸው (ገላ. 3:29)።

የአብርሃም ታሪክ፥ ለአንድ ሰው ወይም ለአንዲት ሴት እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ደስ የሚያሰኝ ግንኙነት ለመመሥረት እንደሚቻል የሚያሳይ አርአያ ነው። አብርሃም የእምነት ጉዞ ምሳሌ ነው። እስራኤላዊም ይሁን ሌላ፥ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ለማድረግ የሚፈልግ ሁሉ፥ በእምነቱ አብርሃምን መምሰል አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃምን በእግዚአብሔር ላይ ጥልቅ እምነት እንዳለው ሰው አድርጎ ያቀርበዋል። እንዲሁም ደግሞ በድካምና በውድቀት እንደ እኛ ዓይነት ሰው እንደሆነም ያሳያል። በአብርሃም ሕይወት ጥናታችን፥ ስለ እምነት ሕይወት ልንማር በምንችላቸው በተለያዩ ርዕሶች ላይ እናተኩራለን።

2ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍ. 12-15 አንብብ።

ሀ) የአብርሃምን የእምነት ጥንካሬ የሚያሳዩትን ነገሮች ዘርዝር።

ለ) በአብርሃም እምነት ውስጥ ድክመት የታየባቸውን ነገሮች ዘርዝር።

ሐ) የአብርሃም ሕይወት ከእምነት ጉዞህ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

3ኛ ጥያቄ፤- ዘፍ. 12፡1-9 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው?

ለ) አብራም መተው የነበረባቸው ሦስት ነገሮች ምንድናቸው?

ሐ) ወዴት መሄድ ነበረበት?

መ) አብራም እንደ ትእዛዙ ከፈጸመ፥ እግዚአብሔር ቃል የገባለትን በረከቶች ዘርዝር።

ሠ) ከአብራም ጋር አብሮ የሄደው ማን ነበር?

ረ) አብራም መጀመሪያ በከነዓን የሰፈረው የት ነበር?

ሰ) ከነዓን ከደረሰ በኋላ፥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው የተስፋ ቃል ምን ነበር?

ሸ) ቀጥሎ አብራም ወዴት ሄደ?

ቀ) አብራም በዚያ ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች ምንድናቸው?

በ) በመጨረሻ አብራም የት ሰፈረ?

1. አብራም በረከቶችን ለማግኘት ሁሉን ትቶ እንዲከተለው እግዚአብሔር አዘዘው (12፡1-23)

አብርሃም ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከ2000 ዓመታት በፊት የነበረ ሰው ነው። አንዳንድ ምሁራን በ2166 ዓ.ዓ. አካባቢ ተወልዶ፥ በ1991 ዓ.ዓ. አካባቢ እንደ ሞተ ይገምታሉ። አብራም የተወለደው ዑር በምትባል ትልቅ ከተማ ውስጥ ነበር። የዑር ከተማ በሥልጣኔ የተራመደች ነበረች። ዳሩ ግን ምግባረ-ብልሹነት የነገሠባት፥ የጣዖት አምልኮ የተንሰራፋባት፥ የረከሰች ከተማ ነበረች። አብራምን ጨምሮ፥ ታራና ቤተሰቡ በዚያው በዑር የጣኦት አምላኪዎች ነበሩ (ኢያሱ 24፡2 ተመልከት)። ምናልባት የሦራ ስም ከጨረቃ አምላክ ሚስት መጠሪያ የተወሰደ ስያሜ ይሆናል። ሆኖም በዚህ በጣዖት አምልኮአቸው መካከል፥ አብራም ዑርን እንዲለቅ በእግዚአብሔር ተጠራ (የሐዋ. 7፡2)። አረማዊው አብራም በእግዚአብሔር በማመን፥ ታዘዘ። ከአባቱ ከታራም ጋር አባቱ እስከ ሞተበት እስከ ካራን ድረስ ተጓዘ።

አብራም በካራን ምን ያህል እንደ ቆየ ባናውቅም፥ ለጥቂት ጊዜ ብቻ የቆየ መሆን አለበት። በኋላ እንደ ተገለጸው፥ አብራም ካራን በለቀቀ ጊዜ በርካታ ንብረትና ሰዎች አግኝቶ ነበር። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ጥሪ አሁንም ወደ አብራም መጣ። እግዚአብሔር የእምነት ጉዞውን የሚያደናቅፉትን ሦስት ነገሮች እንዲተው አዘዘው። በመጀመሪያ፥ አገሩን መተው ነበረበት። ከተወለደባት ከዑር ምድርና ካደገባት የሐራን ምድር የነበረውን ግንኙነት ሁሉ ማቋረጥ ነበረበት። በዚህ ጊዜ ወዴት መሄድ እንደ ነበረበት እግዚአብሔር አልነገረውም ነበር። እግዚአብሔርን በጥንቃቄ በማዳመጥ፥ ወደሚመራው ቦታ መከተል ነበረበት።

4ኛ ጥያቄ፤ - የአገር ፍቅር ለእግዚአብሔር ያለንን እምነትና መታዘዝ እንዴት ያደናቅፈዋል?

ሁለተኛ፥ አብራም ሕዝቡን እንዲተው እግዚአብሔር ነገረው። አብራም ሴማዊ ነበር። ከአንድ ከተለየ ነገድና ጎሳ የተገኘ ሰው ነበር። የነገዱና የጎሳው አባል በመሆኑ፥ ከጠላት ይጠበቅ ነበር። ችግር ቢደርስበት፥ የሚረዱት ሰዎች ነበሩ። ዳሩ ግን አብራም ሕዝቡን እንዲተው ተነገረው። በዚህ ዓይነት ለጥበቃ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ለመደገፍ ተገድዶ ነበር።

ሦስተኛ፥ አብራም የአባቱን ቤት እንዲተው እግዚአብሔር ነገረው። ከሁሉም በላይ አብራም ከዘመዶቹ ጋር የጠበቀ ትስስር ነበረው። ዳሩ ግን እግዚአብሔር እነዚያን ትስስሮች እንዲበጥስና ትቶአቸውም እንዲሄድ ነገረው። አብራም ይህንን በከፊል ብቻ ታዘዘው። የሚች ወንድሙን ልጅ ሎጥን ይዞ እንደ ሄደ እናነባለን። አብራም ለወንድሙ ልጅ ሕጋዊ ኃላፊነት ይኖርበት ወይም አይኖርበት እንደሆነ አናውቅም፤ ዳሩ ግን ሎጥ በኋላ በአብራም ላይ ብዙ ችግር ከማስከተሉም በላይ ከተመረጠው የአብራም የዘር ሐረግ አልተደባለቀም።

5ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እነዚህን ሦስት ነገሮች መተው ለአብራም ከባድ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነበር?

ለ) ከእነዚህ ሦስት ነገሮች ውስጥ ለአብራም ለመተው ይበልጥ የከበደው የትኛው ሊሆን ይችላል?

ሐ) ይህ እግዚአብሔር ከክርስቲያኖች ከሚጠይቀው ጋር እንዴት ይመሳሰላል? (ሉቃ. 14፡25-27፥ 33 ተመልከት)።

መ) ዛሬ ይህን የሚመስል ነገር ለማድረግ እንዴት በእግዚአብሔር እንደተጠራን የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለአብርሃም ምን ማድረግ እንዳለበት ግልጽ ትዕዛዞችን ቢሰጠውም፥ ወዴት እንደሚሄድ አልነገረውም ነበር። ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር የወደፊቱ ነገር ምን እንደሚመስል ለሕዝቡ አያሳይም። ይልቁንም እግዚአብሔር ባሉበት በአሁን ሁኔታ ከእነርሱ ምን እንደሚፈልግ በማሳየት እንዲከተሉት ይጠራል።

ስለ እምነት ሕይወት የምንማረው የመጀመሪያ ትምህርት፥ እምነት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው። አብራም ዑርንና ካራንን ለመልቀቅ ወዲያውኑ አልወሰነም። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ማግኘት ነበረበት። ለትዕዛዙ በእምነት ምላሽ ከመስጠቱ በፊት፥ እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግበት ማወቅ ነበረበት። ዛሬ ብዙ ሰዎች ሰውን የሚያድነው እምነት ብቻ እንደሆነ ያስባሉ። ሁሉም ሰው እምነት አለው። ሙስሊሞችም በአላህና በመሐመድ ያምናሉ። ከሐዲያንም (ኤቲስቶች)፥ እግዚአብሔር እንደሌለ ባላቸው እምነት ላይ ይደገፋሉ። ስለሆነም አስፈላጊው ነገር የእምነት መኖር ወይም አለመኖር ሳይሆን፥ ዳሩ ግን የእምነታችን በእውነት ላይ መመሥረቱ ነው። እምነታችን እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ላይ መመሥረት አለበት። አንድ ወንድ ወይም ሴት እንዴት መዳን እንደሚችል (ትችል) የእግዚአብሔር ቃል ብቻ በትክክል ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ መዳን የምንችለው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሆነ ይናገራል (ዮሐ. 14፡6)። እምነታችን ትክክለኛው ዓለት በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሲሆን ብቻ ስለ ደኅንነት እርግጠኞች ለመሆን እንችላለን።

6ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በግል እምነትህን በኢየሱስ ላይ ያስቀመጥኸው መቼ ነው?

ለ) ያንተ እምነት ከሙስሊሙ፥ ወይም ከሌላ ሃይማኖት ተከታይ እምነት የሚለየው እንዴት ነው?

ከዚህ ታሪክ ውስጥ የምንመለከተው ሁለተኛው ትምህርት፥ እምነት ለማንኛውም ነገር ከሚኖረን ታማኝነት ይበልጥ ለእግዚአብሔር የሚኖረን ታማኝነት መብለጥ እንዳለበት መጠየቁ ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሥፍራ መያዝ አለበት። ከብሔራችን፥ ከዘመዶቻችን፥ ወይም ከቤተሰባችን በላይ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። ልክ አብርሃም አንድ ጊዜ አስፈላጊዎች እንደሆኑ ያስባቸው የነበሩትን ነገሮች ወደ ኋላ መተው እንደነበረበት ሁሉ፥ የእምነት ሕይወት ማለትም ዓለም ወይም ቤተሰባችን ከሚያስተምሩን በተቃራኒ፥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ራሳችንን ሰጥተን፥ ሕይወታችንን ለክብሩ እንሰጣለን ማለት ነው።

7ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት፥ ለሕዝብህ ወይም ለቤተሰብህ ካለህ ፍቅር እንደሚበልጥ በምን መንገድ ሊገለጽ ይችላል?

ለ) ከቤተሰብህና ከእግዚአብሔር አንዱን ለመምረጥ የተገደድህበት ጊዜ ነበር? ከሆነ፥ ማንን እንደመረጥህ ተናገር።

እግዚአብሔር አብራምን እንዲተው ማዘዝ ብቻ ሳይሆን፥ ከታዘዘ በሰባት በረከቶች እንደሚጎበኘውም ተስፋ ሰጥቷል። ‹በረከት› የሚለው ቃል ሁለቱንም ሥጋዊና መንፈሳዊ በረከቶች ያመለክታል።

1. ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ። እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠው የመጀመሪያው የተስፋ ቃል ታላቅ ሕዝብ የማድረግ ነበር። የአብርሃም ቤተሰቦች በርካታ መሆን ብቻ ሳይሆን፥ ሕዝብ በመሆንም መደራጀት ነበረባቸው። ይህ የተስፋ ቃል የአብራም የሥጋ ልጆች የሆኑት የእስራኤል ሕዝብ በሙሴና በኢያሱ መሪነት ታላቅ ሕዝብ ለመሆን በበቁበት ጊዜ ተፈጽሞአል።

2. እባርክሃለሁ። ይህ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሚያስፈልጉትን ነገሮች እንደሚያሟላ የገባለት የተስፋ ቃል ነው። በሥጋዊ ኑሮው ቁሳቁሳዊ ብልጽግና በመስጠት ይባርከው ነበር። እንዲሁም እርሱን በመጠበቅና በጠላቶቹ ላይ ድል በመስጠት ይባርከው ነበር (ዘፍ. 14)። በመንፈሳዊ ነገሮችም ይባርከው ነበር።

3. ስምህን አከብረዋለሁ። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ አብርሃም የሦስት አበይት ሃይማኖቶች አባት ነው - የአይሁዶች፥ የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች። በእነዚህ በኩል ስሙ ታላቅ ሆኗል። በዘመኑም እንኳ፥ በከነዓን በነበሩት ሌሎች ሰዎች ዘንድ እንደ ንጉሥ እስኪታይ ድረስ፥ አብርሃም የገነነ ዝና ነበረው (ዘፍ. 23፡6)። የባቢሎንን ግንብ ይሠሩ የነበሩ ሰዎች፥ በሠሩት ሥራ የራሳቸውን ስም ገናና ለማድረግ ፈለጉ። ዳሩ ግን እውነተኛ ዝና የሚመጣው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። ይህም ሰውዬው ለእግዚአብሔር ለሚያሳየው እምነትና መታዘዝ ሽልማት ሆኖ የሚሰጥ ነው።

8ኛ ጥያቄ፤ - በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ዝነኛ በመሆንና በዓለም ፊት ዝነኛ በመሆን መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

4. ለበረከት አደርግሃለሁ። እግዚአብሔር አብራምን እንደሚባርክ ብቻ ሳይሆን፥ በእርሱ ሌሎችም እንደሚባረኩ የተስፋ ቃል ገብቶለታል። ይህ በብዙ መንገዶች ተፈጽሟል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው፥ በአብራምና የእርሱ ትውልዶች በሆኑት አይሁዶች በኩል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በአይሁዶች ነው። የዓለም የግብረ-ገብነት መመሪያ የሆኑት አስርቱ ትዕዛዛት ለዓለም የታወቁት በአብራም ትውልዶች በኩል ነበር። እነዚህ በአብራም በኩል ወደ ዓለም ከመጡት በረከቶቹ ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው።

5. የሚባርኩህን እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማለሁ። ሰዎች ከእርሱ ጋር ከሚኖራቸው ግንኙነት አኳያ እንደሚባረኩ፥ ወይም እንደሚረገሙ እግዚአብሔር ለአብራም ቃል ገብቶለታል። ሎጥን በተዋጉት ሰዎች ላይ አብራም ያገኘው ድል እንዴት በአንድ በኩል የዚህ የተስፋ ቃል ፍጻሜ እንደሆነ እንመለከታለን። አያሌ ክርስቲያን የታሪክ ጠበብት፥ ይህ ቃል ኪዳን በታሪክ ውስጥ ሲፈጸም ታይቷል ይላሉ። አይሁዶችን የጠሉና የአብራምን ትውልዶች ለማሳደድ የፈለጉ ሕዝቦች በተራቸው ጠፍተዋል። ለምሳሌ፥ ባቢሎንንና አሦርን ለአብነት ይጠቅሳሉ። ዳሩ ግን አይሁዶችን የተንከባከቡና ያከበሩ ሕዝቦች በቁሳዊ ሀብት፥ በሰላም፥ ወዘተ. ተባርከዋል። ዛሬ በዓለም ላይ፥ በብዙ ሕዝቦች መካከል ፀረ-ይሁዲ የሆነ ስሜት

ይታያል። ይህ በአብራም የተነሣ ለእግዚአብሔር ልዩ የሆኑትን የአይሁድ ሕዝቦች ለማጥፋት ሰይጣን ያለው መሻት ምሳሌ ነው።

ከዚህ ሁሉ በላይ ግን፥ አብራምን የሚያከብሩና በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን የእምነት ፈለግ የሚከተሉ ሰዎች፥ እነርሱም በእምነት ስለሚራመዱ ይባረካሉ። ዳሩ ግን አብራምንና እምነቱን የማያከብሩ ሰዎች፥ የበረከት መንገድ ከሆነው እምነት እራሳቸውን አግልለዋል። በረከት ሊመጣ የሚችለው በእግዚአብሔር ላይ ባለ እምነት ብቻ ነው። ስለሆነም ያንን እምነት የጣለ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን እርግማንና ፍርድ ይቀበላል።

9ኛ ጥያቄ፤ - ይህ የተስፋ ቃል ዛሬ ለእኛ እውነት የሚሆነው እንዴት ነው?

6. የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ። እግዚአብሔር ለአብራምና የእርሱ ትውልዶች ለሆኑት አይሁዶች ብቻ አልገደደውም። ይልቁንም እግዚአብሔር ለፈጠራቸው ሰዎች ሁሉ ይገደዋል። እግዚአብሔር አብራምንና አይሁዶችን የመረጠው፥ እነርሱን ለመባረክ ብቻ ሳይሆን፥ ዳሩ ግን በእነርሱና በምስክርነታቸው በኩል፥ ሰዎች ሁሉ ፈጣሪ አምላክ የሆነውን የእስራኤልን ቅዱስ ወደ ማወቅ እንዲደርሱ ነው። እስራኤል ለአሕዛብ ብርሃን፥ ለዓለም ካህን መሆን ነበረባት (ዘጸ. 19፡5-6 እና ኢሳ. 42፡6 ተመልከት)። ሆኖም ብዙውን ጊዜ እስራኤላውያን ለዓለም ብርሃን ስላልሆኑ፥ ይህ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከፍጻሜ አልደረሰም። እንደ ሌሎቹ የዓለም ሕዝቦች ሁሉ እነርሱም ክፉዎች ነበሩ። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በእስራኤሎች በኩል ስለ ነበር፥ ይህ የተስፋ ቃል በከፊል ተፈጽሟል።

10ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ከእነዚህ በረከቶች ውስጥ ዛሬ ለእኛ ቃል የተገቡት የትኞቹ ናቸው?

ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጸሙት እንዴት ነው?

ዘፍጥረት 12፡2-3 ከአብርሃም ጋር ለተደረገው ቃል ኪዳን መሠረት ነው። ይህ ቃል ኪዳን በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እየተደጋገመና እየተስፋፋ ይሄዳል (ምዕ. 15፥ 17፥ ወዘተ.)።

ቀጣዩ የእምነት ሕይወት መመሪያ፥ እግዚአብሔር በእምነት ለሚመላለሱ ሰዎች ሁል ጊዜም ታላላቅ በረከቶችን ለመስጠት ቃል እንደሚገባ ነው። ምንም እንኳ ሀብታም ባንሆንና እንደ አብራምም የአዲስ ሕዝብ አባት ላንሆን ብንችልም፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ካመንን የዘላለም ሕይወትና የዘላለም ሽልማቶች በሰማያት እንደሚጠብቁን ጽኑ የተስፋ ቃል አለን (ኤፌ. 1፡3-14)። አብርሃም ተስፋ የተሰጡትን ሽልማቶች ለማግኘት፥ እግዚአብሔር በተስፋ ቃሉ የተናገረውን ነገር እንደሚፈጽም ማመንና በታዛዥነት መሥራት ነበረበት።

2. የአብርሃም እምነት ለእግዚአብሔር በመታዘዙ በግልጽ ታይቷል (12፡4-6)።

አብራም በሁለት ምርጫዎች መካከል ተፋጠጠ። ምቹ፥ የተሰናዳና አስተማማኝ ሕይወት እየመራ፥ ከቤተሰቡና ከዘመዶቹ ጋር በቤት መቀመጥ፥ ማለትም ቀላሉን መንገድ መከተል፥ ወይም እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃል በመቀበል፥ ሁሉንም ትቶ እግዚአብሔርን በእምነት መታዘዝ ነበረበት። ካራንን እንዲለቅ እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዝ በመቀበል ከታዘዘ የሚጠብቀውን የበረከት የተስፋ ቃል በመያዝ፥ አብራም የእምነት ጉዞውን በመጀመር ታዘዘ። ቤተሰቡን ሚስቱን ሦራን፥ የወንድሙ ልጅ ሎጥን፥ ባሪያዎቹንና ያለውን ንብረት ሁሉ በመያዝ ረጅሙን ጉዞ ወደ ከነዓን ምድር ተያያዘው። አንዳንድ ሊቃውንት «ያገኙአቸውን ሰዎች» የሚለው ቃል የሚያመለክተው፥ ባሪያዎቹን ወይም አገልጋዮቹን ሳይሆን፥ ከአብራም ጋር በመሄድ እውነተኛውን አምላክ ለመከተል የፈለጉትን የተለያዩ ሰዎች እንደሆነ ያስባሉ። በአብራም ምስክርነት አማኞች ሆኑ። ከነዓን በደቡብ አቅጣጫ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮች የሚቆጠር ርቀት ላይ ያለች፥ ረዥም ጉዞ የምትጠይቅ አገር ነበረች። ምንም እንኳ አብራም ወደ እርጅና የተቃረበ ቢሆንም (75 ዓመታት)፥ ጌታን በመታዘዝ ሁሉንም ተወ። ወደ 2080 ዓ.ዓ. አካባቢ ከነዓን ደረሰ።

11ኛ ጥያቄ፥- ከዚህ ስለ እምነት የምትመለከተው ትምህርት ምንድነው?

ሌላው የምንገነዘበው የእምነት ሕይወት መመሪያ: እነዚያ በእምነት የሚመላለሱ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን በረከቶች ለመቀበል: ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት መታዘዝ እንዳለባቸው ነው። አብራም ባይታዘዝና በካራን ቢቀር ኖሮ፥ እግዚአብሔር ተስፋ የሰጣቸውን በረከቶች ሁሉ አይቀበልም ነበር። የእግዚአብሔርን የተስፋ ታሪኮች ማወቅ አይበቃም። ወንጌሉን ማወቅ ብቻ አይበቃም። እምነት ወደ መታዘዝ እስካልመራ ጊዜ ድረስ፥ እውነተኛ እምነት አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን እንደተቀበልን የምንናገር ከሆነ፥ ትዕዛዛትን በመጠበቅ እምነታችንን ማሳየት አለብን (ዮሐ. 14፡23)።

12ኛ ጥያቄ፤- ሀ) ክርስቲያኖች መታዘዝ ያለባቸውን ቢያንስ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዛት ዘርዝር።

ለ) አንተ እንዴት እየታዘዝሃቸው እንዳለህ ግለጽ።

በዘፍጥረት 12፡6፥ ሙሴ ለአብራምና ለእስራኤላውያን የእምነት ጉዞ አደገኛ በሆኑት ነገሮች ላይ ፍንጭ ይሰጣል። በመጀመሪያ፥ አብራም በ «ሞሬ የአድባር ዛፍ» እንደ ሰፈረ ይናገራል። በጥንት ጊዜ፥ ትላልቅ ዛፎች ብዙውን ጊዜ የባዕድ አምልኮ የሚካሄድባቸው ሥፍራዎች ነበሩ። ምናልባት ይህ ዛፍ ከነዓናውያን ስለ ባዕድ ሃይማኖታቸው ለመማር የሚሰባሰቡበት፥ ወይም የከነዓን ካህናት ከአማልክቶቻቸው ምሪት ለማግኘት የሚማልዱበት ሥፍራ ይሆናል። አብራም የተጋፈጠው የመጀመሪያው አደገኛ ሁኔታ፥ በእውነተኛው አምላክ ላይ የነበረው እምነቱ፥ በሐሰተኛ ሃይማኖቶች መበረዝ ነበር። ይህ በኋላ እስራኤላውያንን ካጋጠሙዋቸው አበይት ችግሮች አንዱ ሲሆን፥ ሙሴም ይህንኑ በማስመልከት በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እየሰጣቸው ነበር።

13ኛ ጥያቄ፤- ሀ) ይህ አደገኛ ሁኔታ ዛሬ በክርስቲያኖች መካከል የሚገኘው እንዴት ነው?

ለ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባላት የሰይጣን ወጥመድ በሆኑት የሐሰት ትምህርቶች የሚጠመዱት እንዴት ነው?

አብራም የተጋፈጠው ሁለተኛው አደገኛ ሁኔታ ከከነዓናውያን አቅጣጫ ነበረ። ከነዓናውያን የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የሚሆኑ ሰዎች ነበሩ። እስራኤላውያንን አንድም በጦርነት (በስደት) በማሸነፍ፥ አለበለዚያም በጋብቻ በመሳብ ለመርታት ይሹ ነበር። በእምነት ለመጓዝ ለሚፈልጉ ሰዎች ሁል ጊዜም ጠላቶች አሉዋቸው። አማኞችንም በተመሳሳይ ሁለት መንገዶች ይዋጉዋቸዋል። ባመዛኙ ቀጥተኛ ስደት ያመጣሉ። ዳሩ ግን ይበልጥ አደገኛ የሚሆነው፥ አማኞቹ እነርሱን እንዲመስሉ በማግባባት፥ ሕይወታቸውን ለማበላሸት መፈለጋቸው ነው።

14ኛ ጥያቄ፤ - ሰይጣን የእምነት እርምጃህን ለማበላሸት፥ በሕይወትህ እነዚህን ሁለት ዘዴዎች እንዴት እንደ ተጠቀመባቸው ግለጽ።

3. እግዚአብሔር ለአብራም የሰጠውን የተስፋ ቃል መልሶ ያጠናከረዋል (12፡7)።

የአብራምን እምነትና እርሱን ለመከተል ብሎ ሁሉን በመተው ያሳየውን መታዘዝ በመመልከት፥ አብራም ከነዓን በደረሰ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንደገና አጠናከረው። ቃሉን ብቻ በመላክ ፈንታ፥ እግዚአብሔር እራሱን በራእይ ለአብራም ሲገልጽ ለመጀመሪያ ጊዜ እንመለከታለን። እግዚአብሔር አብራምን በእምነት ጉዞው ለማበርታት ፊት ለፊት ተገናኘው። በቀደሙት 6 በረከቶች ላይ፥ እግዚአብሔር አሁን አንድ ሌላ የተስፋ ቃል አከለለት።

7. ይችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ርስት አድርጎ እንደሚሰጠው ለአብራም የተስፋ ቃል ሰጠ። ምድሪቱ ቃል የተገባችው በግልጽ ለአብራም ትውልዶች እንደመሆኑ ሎጥ የአብራምን የተስፋ ቃሎች አይወርስም ነበር።

4. አብራም መሠውያ በመሥራት እግዚአብሔርን አመለከ (12፡7-9)።

አብራም በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት፡ በአምልኮ ገለጸ። አብራም መሠውያ የሠራባቸው ሥፍራዎች፡ የመገናኛ ድንኳኑ ከመሠራቱ በፊት በብሉይ ኪዳን የአምልኮ ቦታዎች ነበሩ። በመሠዊያዎቹ ላይ፡ አብራም ለእግዚአብሔር ያለውን ምስጋናና መሰጠት በመግለጽ፥ እንስሳትን ሠዋ።

አብራም የተቀደሰውን ዛፍ በመተው፡ በደቡብ ጫፍ ወደሚገኘው የከነዓን ምድር ተጓዘ። በመጀመሪያ በከነዓን መሀል ወደሚገኘው ቤቴል ሄደ። በዚያም ደግሞ ለእግዚአብሔር መሠውያ ሠራ። መሠውያ መሥራት ብቻ ሳይሆን፥ «የእግዚአብሔርንም ስም ጠራ»። ይህ የግል አምልኮትን ብቻ የሚያመለክት አይደለም። ይልቁንም በእግዚአብሔር ማመኑንና እርሱን መከትሉን ለሰው ሁሉ ያወጀበት ነበር። በዚህም አድራጎቱ፥ አብራም መስበክ ወይም እግዚአብሔር ማን እንደ ሆነ በይፋ ማወጅ እንደ ጀመረ አድርገን መውሰድ እንችላለን። ከአብራም የተነሣ፥ በዚያ አካባቢ የነበሩ ሰዎች ሁሉ እውነተኛው አምላክ ማን እንደሆነ ሰምተዋል።

15ኛ ጥያቄ፤- «የእግዚአብሔርን ስም» ለጎረቤቶችህ በምን በምን መንገዶች ታውጃለህ?

መጽሐፍ ቅዱስ «የእግዚአብሔር ስም» በሚለው አገላለጽ የተጠቀመው እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ስም ለመጥቀስ ሲል ነው እንደ ሆነ ነው። አብራም ያለምክንያት ብድግ ብሎ ኤሎሂም ወይም ጁፒተር ወይም ያህዌ በማለት የእግዚአብሔርን ስም አልጠራም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ ሁል ጊዜም የአንድ ሰው ስም ባሕርዩንና ማንነቱን የመለክታል። አብራም የእግዚአብሔርን ስም በጠራ ጊዜ፥ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ማለትም፥ ስለ ፍቅሩ፥ ስለ ፍርዱ፥ ስለ ባርማው፥ ስለ ፈጣሪነቱ፥ ወዘተ. ሰበከ ማለት ነው።

ይህ ልብ ልንለው የሚያስፈልገን ነገር ነው። በምንጸልይበት ጊዜ፥ መዛኙ «በኢየሱስ ስም» እንጸልያለን። ኃይሉ የሚመጣው ኢየሱስ የሚለው ስም አይደለም። በአዲስ ኪዳን ዘመንና ዛሬም «ኢየሱስ» የሚል ስያሜ ያላቸው በርካታ ሰዎች አሉ። ዳሩ ግን የኢየሱስ ስም ወደ ኢየሱስ ባሕርያት ማለትም አዳኝ፥ የነገሥታት ንጉሥ፥ የሁሉም ገዥ

ወደ መሆኑ ያመለክታል። ኃይሉ ያለው ኢየሱስ የሚለውን ስም ከያዘው አካል እንጂ፥ ኢየሱስ ከሚለው ስም ከራሱ አይደለም።

16ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) አንዳንድ ሰዎች በሚጸልዩበት ጊዜ ወይም በጸሎታቸው ማብቂያ ላይ ኢየሱስ የሚለውን ስም ድምፃቸውን አጉልተው የሚጠሩት ለምንድነው?

ለ) ጸሎታችንን «በኢየሱስ ስም» ብለን የምንፈጽመው ለምንድነው?

ሐ) ይህን ስናደርግ፥ ዓላማችን ምንድነው?

ከዚያም አብራም፥ በደቡብ ከነዓን ወደሚገኘውና ብዙ ከነዓናውያን ወዳልሠፈሩበት ወደ አዜብ (ኔጌብ) ተጓዘ። ከፊል በረሃማና ለከብት እርባታ ብቻ የሚስማማ አካባቢ ነበር። ይህ በከነዓን ምድር ዋና ሠፈሩ ሆነ። ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስ፥ አብራም በድንኳን ውስት እንደኖረ ስለሚናገር፥ ይህ በእርግጥ ቋሚ ቤቱ አልነበረም። አብራም ልቡ በሰማያዊ ነገሮች ላይ ስላተኮረ፥ ቤት ሳይኖረው ከቦታ ወደ ቦታ የሚጓዝ መናኝ ነበር።

17ኛ ጥያቄ፤ ዕብ. 11፡8-16 አንብብ።

ሀ) አብርሃም ተስፋ በተሰጠው ምድር እንደ እንግዳ ሆኖ እንዲኖር ያደረገውና የሚጠብቀውስ ነገር ምን እንደነበር ጸሐፊው ምን ሲል ይነግረናል?

ለ) ከእዚህ ውስጥ፥ በእዚህ ምድር ላይ ስለሚኖረን ጉዞ ምን እንማራለን? (1ኛ ጴጥ. 2፡11 ተመልከት)።

ስለ እምነት ጉዞ የምንመለከተው የመጨረሻው ነገር፥ እምነት እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ እንደሚመራ ነው። አብራም እግዚአብሔርን መታዘዝ ብቻ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ላይ የመደገፍም ሕይወት ነበረው። እግዚአብሔርን በማምለክ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅርና በእግዚአብሔር ላይ ያለውን መደገፍ አሳይቷል።

18ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ዛሬ ስለ እምነት ጉዞ የተማርናቸውን ትምህርቶች ከልስ።

ለ) እነዚህስ ዛሬ ከእኛ ከሚፈለግብን እምነት ጋር የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

በእዚአብሔርና በአብራም መካከል የተደረገው የመጀመሪያው ቃል ኪዳን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሚገኙት ሌሎች ቃል ኪዳኖች ሁሉ መሠረት ይጥላል። እነዚህን ቃል ኪዳኖች በዛሬው ጊዜ እንዴት እንደምንጠቀምባቸው መጠንቀቅ አለብን። ሁለት ነገሮችን ማስታወስ ያሻል። በመጀምሪያ፥ ለአብራም ከተሰጠው ቃል ኪዳን የሚበዛው ክፍል የአብራም ትውልዶች በሆኑት አይሁዶች በሥጋዊ ሁኔታ መፈጸም ነበረበት። ዛሬ በቀጥታ በቤተ ክርስቲያን ላይ ልንጠቀምባቸው አንችልም። እግዚአብሔር፥ የብሉይ ኪዳንን ታሪክ ለመረዳት መሠረት የሚጥሉ ሁለት የተስፋ ቃሎችን ለአብራም ሰጥቷል።

ሀ. እግዚአብሔር ከአብራም ትውልዶች ውስጥ ትልቅ ሕዝብ ለማዘጋጀት ቃል ገብቷል። ይህ በእስራኤል ሕዝብ ተፈጽሟል።

ለ. እግዚአብሔር ከነዓንን ለእስራኤል ለመስጠት ቃል ገብቷል። ይህ በሙሴና በኢያሱ መሪነት ተፈጽሟል።

ሁለተኛ፥ የእግዚአብሔር መሻት አይሁዶችን ብቻ ሳይሆን፥ ሰዎችን ሁሉ መባረክ ነበር። ሁላችንም፥ አብራም የነበረው ዓይነት እምነት ካለን፥ ከአብራም ጋር በተደረገው ቃል ኪዳን ውስጥ የተገለጹትን መንፈሳዊ በርከቶች እንቀበላለን።

ምሁራን እነዚህ የተስፋ ቃሎች ወደ ፊት ስለሚፈጸሙበት ሁኔታ አይስማሙም። አይሁዶች በ70 ዓ.ም. አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ሲሆን፥ እስከ 1948 ዓ.ም. ድረስ መንግሥታቸውን መልሰው አልመሰረቱም ነበር። አይሁዶች ዛሬ በእስራኤል ምድር ላይ ያላቸው መብት እግዚአብሔር ለአብራም በሰጠው የተስፋ ቃል ላይ እንደተመሠረተ ይናገራሉ። አንዳንድ ምሁራን፥ አይሁዶች ኢየሱስን ስላልተቀበሉ፥ እነዚህ ለአብራም የተሰጡት ሥጋዊ የተስፋ ቃሎች ለእነርሱ አይሠሩም ይላሉ። የበረከቱ ተቋዳሽ የሚሆኑትም የአብራም መንፈሳዊ ልጆች የሆኑት አማኞች እንደሆኑ አሳምረው ያስተምራሉ። እነዚህ የተስፋ ቃሎች በመንፈሳዊ ሁኔታ ለቤተ ክርስቲያን የሚሠሩ ናቸው ይላሉ።

ዳሩ ግን እነዚህ ከእግዚአብሔር የተሰጡ የተስፋ ቃሎች ዘላለማዊ ነበሩ። ስለዚህ በአብራም ሥጋዊ ትውልዶች ትዕዛዝ መተላለፍ ለዘላለም ሊታጠፉ አይችሉም ነበር። በርካታዎቹ የብሉይ ኪዳን ነቢያት፥ ሥጋዊው የእስራኤል መንግሥት መቼ እንደሚመለስና የዳዊትም ልጅ በእነርሱ ላይ መቼ እንደሚገዛ ጊዜውን ይተነብያሉ። ሌሎች ክርስቲያኖች ይህ ገና መፈጸም እንዳለበት ያስባሉ። የሚፈጸመውም ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የሺህ ዓመታት መንግሥቱን ለመመሥረት ሲመለስ እንደሆነ ይናገራሉ።

በዚህ ታሪክ፥ ሙሴ ለእስራኤላውያንም ሆነ ለእኛ፥ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት፥ እንደ አብራም መሆን እንዳለብን ለማሳየት ይፈልጋል። መባረክ የምንችለው እግዚአብሔር ሲያዘንና እኛም ስንታዘዝ ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ማንኛውም ዓመፅ የእግዚአብሔርን በረከት ከእኛ ላይ ያርቀዋል። ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለመረዳትና ለመታዘዝ ሊያስቸግር ቢችልም፥ በእምነት ተቀብለን እንድንታዘዘው ይጠይቃል። እነዚያ እግዚአብሔርን ለማክበር የሚሹ ሰዎች፥ ዓለም ብትሳለቅባቸውም እንኳ፥ ሁሉንም ለእግዚአብሔር ትተው ያመልኩታል።

19ኛ ጥያቄ፤ - ሕይወትህን መርምር። እምነትህ እንደ አብርሃም ዓይነት ነው? አብራራ። ካልሆነ፥ እግዚአብሔር እምነትህን እንዲያሳድግልህ ዛሬ ጠይቅ።

ሁለተኛ ቀን- ዘፍጥረት 12፡10-13፡16

በእምነት ለመጓዝ የሚወስኑ ሰዎች የሚጋፈጧቸው ሁለት ፈተናዎች አሉ። በመጀምሪያ፥ የታማኝነት ፈተና አለ። ሰይጣን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ጥሩ ስም ለማጥፋት ይፈልጋል። ጥሩ ስማቸው ከጠፋ፥ ምስክርነታቸውም ጠፋ ማለት ነው። ይህ የታማኝነት ፈተና ብዙውን ጊዜ እራሳችንን ለመጠበቅ በምናደርገው መዋሸት ይከሰታል። በምንዋሸበት፥ ወይም እግዚአብሔርን ሳንጠይቅ አንድን ነገር ለማድረግ በምንሻበት ጊዜ የእምነትን ፈር በመልቀቅ የእራሳችንን መሥመር እንይዛለን። ይህም የእራስ መሥመር ወደ ታላላቅ ችግሮች ሊያመራን ይችላል።

ሁለተኛው ፈተና የሀብትና የቁሳቁስ በረከት ፈተና ነው። ብዙውን ጊዜ ሀብታም ለመሆንና ቁሳቁስ ለማከማቸት የሚደረገው መሯሯጥ እግዚአብሔርን ወደማያስከብር ምርጫ ይመራል። ሀብት ለእግዚአብሔር ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት እጅግ አደገኛ ከሆኑት ነገሮች አንዱ ነው። ሀብት ለማከማቸት ከሚደረግ ሩጫ የእምነትን ሕይወት መኖር አስቸጋሪ ነው። ዛሬ አብራም እንዴት እነዚህን ሁለት ችግሮች እንደተጋፈጣቸው እንመለከታለን።

20ኛ ጥያቄ፤ ሀ) እነዚህን ሁለተ ፈተናዎች በራስህ፥ ወይም የቤተ ክርስቲያንህ መሪ በሆነ ሰው ሕይወት ውስጥ እንዴት እንዳየሃቸው ግለጽ።

ለ) ክርስቲያን መሪዎች እነዚህን ሁለት ነገሮች ማወቅና ከእነርሱም መንጻት የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

አብራም የእምነት ጉዞውን በትልቅ እርምጃ ጀመረ። በፊት የባዕድ አምልኮ ተከታይ የነበረውና፥ ስለ እግዚአብሔር ጥቂት ብቻ ያውቅ የነበረው አብራም ሐራንን እንዲለቅ የሚናገረውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሰምቶ ታዘዘ። ጉዞውም ወደ ከነዓን ደቡብ ክፍል መራው። ምንም እንኳ አብራም የእምነት ጉዞውን በጥሩ ሁኔታ ቢጀምርም፥ ይህ ማለት ግን ሁል ጊዜም በእምነት ተጉዞአል ማለት አይደለም። ዛሬ ስለ አብራም ሁለት ታሪኮችን እናጠናለን። አንደኛው እምነት ማጣቱን ሲያሳይ፥ ሁለተኛው በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን ታላቅ እምነት ያመለክታል። አብራም በእምነት ጉዞአችን፥ ልክ እንደ እኛ ዓይነት ሰው ነበር። ወደ እግዚአብሔር የምንጠጋባቸውና በታዛዥነት የምንራመድባቸው፥ ወደ ተራራ ጫፍ ላይ የሚያመሩ ጊዜያት አሉ። እንዲሁም ሁላችንም በእምነት ጉዞው የምንደናቀፍባቸው፥ ቁልቁል ወደ ሸለቆ የምንወርድባቸውም ጊዜያት አሉ። ይሁንና በተራራ ላይ ሆነን በምንፈነጭባቸው ጊዜያትም ሆነ፥ በሸለቆ ሕይወታችንም ውስጥ እግዚአብሔር ታማኝ ወዳጃችን ነው።

በዛሬው ትምህርታችን የምናጠናቸው ሁለት አበይት ታሪኮች ስላሉ፥ ትምህርቱን በሁለት ክፍሎች እንከፍለዋለን። በመጀመሪያ፥ አብራምና ሦራ ወደ ግብፅ ያደረጉትን ጉዞ እንመለከታለን (12፡10-20)።

21ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 12፡10-20 አንብብ።

ሀ) አብራምና ሦራ ለምን ወደ ግብፅ ወረዱ?

ለ) አብራም ወደ ግብፅ በገባ ጊዜ የፈራው ነገር ምን ነበር?

ሐ) አብራምና ሦራ የነበራቸው ዕቅድ ምን ነበር?

መ) በሦራ ላይ ምን ደረሰ?

ሠ) ንጉሡ መጀምሪያ በአብራም ላይ የነበረው አመለካከት ምን ነበር?

ረ) እግዚአብሔር ሦራን እንዴት ጠበቃት?

ሰ) በመጨረሻ በአብራም ላይ የደረሰው ነገር ምን ነበር?

ሸ) አብራምና ሦራ እምነታቸውን አሳዩ ወይስ አላሳዩም? ለመልሶችህ ምክንያቶችን ስጥ።

ቀ) እንዴት መሆን ይገባችው ነበር ትላለህ?

ትናንትና የአብራምን ጥሪና እግዚአብሔር የሰጠውን የተስፋ ቃሎች አጥንተናል። እነዚህ የተስፋ ቃሎች በሁለት አስፈላጊ እውነቶች ላይ የተመሠረቱ ነበሩ። በመጀመሪያ፥ አብራም በሦራ በኩል ዘር ሊያገኝ ይገባ ነበር። ሁለተኛ፥ አብራም የከነዓንን ምድር መውረስ ነበረበት። ሰይጣን፥ እግዚአብሔር ከአብራም ጋር የገባቸውን እነዚህን ሁለት የቃል ኪዳን መሠረቶች ለማጥፋት፥ ሁለት አበይት ፈተናዎችን እንዴት እንደ ተጠቀመ በዛሬው ትምህርታችን እንመለከታለን።

አብራም በከነዓን ምድር በምትገኘው አዜብ (ኔጌብ) ውስጥ ምን ያህል እንደ ቆየ አናውቅም። ዳሩ ግን በከነዓን ምድር ረሃብ ተነስቶ እንደነበረ ተገልጾልናል። ረሃብ በከነዓን ተደጋግሞ የሚደርስ ሲሆን፥ በአባይ ወንዝ ዳርቻ በግብፅ ውስጥ ግን ሁል ጊዜም ምግብ ነበረ። ከረሃቡ ለማምለጥ ወደ ግብፅ መውረድ ለአብራምና ለሦራ ተገቢ ሊመስላቸው ይችላል። በሕይወት ለመሰንበትና ትውልድ ለማፍራት ከተፈለገ፥ ከረሃብ ማምለጥ እንደ ነበረባቸው ሳይገነዘቡ እንደማይቀሩ ጥርጥር የለውም። ዳሩ ግን፥ ምንም እንኳ ከአብራምና ከሦራ ነጥብ ስንነሣ ተገቢ ቢሆንም፥ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እግዚአብሔርን

ስለመጠየቃቸውና ስለማማከራቸው የቀረበ መረጃ የለም። በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ፈንታ፥ አብራምና ሦራ ወደ ግብፅ ወረዱ።

እግዚአብሔር እንዲመራቸው ስላልጠየቁ፥ ወዲያውኑ እራሳቸውን በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ከትተው ተገኙ። በባዕድ አገር ውስጥ እንግዶች ነበሩ። የግብፅ ምድር መብት ለሌላቸውና መጠጊያ ላጡ እንግዶች በጨካኝነቱ የታወቀ ነበር። አብራም ይህን ተገንዝቦአል። ስለሆነም እራሱን ለመጠበቅ፥ ሦራን እህቱ እንጂ ሚስቱ እንዳልሆነች እንድትናገር መከራት። ይህንንም ያደረገው ሦራ አሮጊትም ብትሆን (65 ዓመታት ዕድሜ ያላት)፥ ውብ ስለ ነበረች ነው። በባዕድ ምድር መብት ስላልነበራቸው፥ ባልና ሚስት መሆናቸውን ሰዎች ቢያውቁ፥ ሦራን ለመውሰድ ብለው አብራምን ይገድሉት ነበር። አሁንም እግዚአብሔር እንዲመራቸው ወይም እንዲጠብቃቸው አልጸለዩም ነበር። በእግዚአብሔር ላይ በእምነት ከመደገፍ ይልቅ፥ የእራሳቸውን እቅዶች አወጡ። እነዚህም እቅዶች በውሸት ላይ የተመሠረቱ ነበሩ። ከፊል እውነት በመናገር፥ ሰዎች ውሸትን እንደሚያምኑላቸው ያውቁ ነበር። ሦራ የአብራም አባት ከሌላ ሴት የወለዳት፥ ግማሽ እህቱ ነበረች (ዘፍ. 20፡12 ተመልከት)። ዳሩ ግን ተጋብተው ነበር። በእኛ ምትክ እግዚአብሔር እንዲሠራ በመፍቀድ ፈንታ፥ ዛሬ ብዙዎቻችን እንደምናደርገው፥ አብራም እራሱን ለመጠበቅ ሲል ዋሸ። ሆኖም ሦራን ከአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንደከተታት አላስተዋለም ነበር። የሦራ በሌላ ሰው መወሰድና በእርሷም በኩል ልጅ እንደሚያገኝ እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ግድ አልነበረውም። ስለራሱ ብቻ አሰበ። በመሆኑም ራሱን ለመጠበቅ ዋሸ።

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንዳንድ ክርስቲያኖች በዛሬ ጊዜ ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የሚዋሹት እንዴት ነው? ይህስ ትክክል ይመስልሃል?

ለ) አብርሃም በዋሸ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳለው አሳየ ወይንስ አላሳየም? አብራራ።

ሐ) ራሳችንን ለመጠበቅ ለሰውስ መዋሸት ጥሩ ነውን? ለምን?

በግብፅ ከደረሱ ብዙም ሳይቆይ፥ የሦራን ቁንጅና የሚያበስረው ዜና ተሰራጨ። ንጉሡ ስለ እርስዋ ሰማና ወደ ቤቱ ወሰዳት። ሚስት ለማግኘት ከአብራም ጋር የተለመደ የስምምነት ዘዴ እንደተከተለ የሚያመለክት መረጃ የለም። ከፈርኦን ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ስለ መፈጸሟ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም፥ እግዚአብሔር ስለ ጠበቃት ይህ ያልሆነ ይመስላል።

ለአብራም ትውልድ ለመስጠት የተደረገው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ምን ይሆን እንደ ነበር ልብ በል። በዚያን ጊዜ ልጆች የምትወልድለት ሚስቱ ተወስዳበት ነበር። ከአብራም አለማስተዋልና እምነት ማጣት የተነሣ፥ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ሊጠፉ ነበር።

አንድ ሌላ ነገር አስተውል። አብራም የፈለገውን አግኝቷል። ሕይወቱ ከመትረፉም ሌላ ሀብታም ሆኗል። አብራም እምነት በማጣቱ ተጠቅሟል። ፈረኦን ብዙ ነገሮች ስለ ሰጠው አብራም ሀብታም ሆነ። ስጦታው ምናልባት ጥሎሽ ይሆናል። ብዙ ክርስቲያኖች፥ ሀብት ካገኘን እግዚአብሔር እየባረከን ነው ብለው ያስባሉ። ሀብት የግድ የበረከት ምልክት አይደለም። አብራም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ነበር፤ የሚኖረውም ያለ መታዘዝን ሕይወት ነበር፤ ዳሩ ግን የቁሳቁስ ሀብት እያገኘ ነበር። ተገቢ ያልሆኑ ልምምዶች በመጠቀም ሀብታም ለመሆን ቢቻልም፥ ዳሩ ግን ይህ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስከትላል። የእግዚአብሔርን ባርኮት ካጣ፥ የአብራም ሀብት ለምን ይረባል?

ሦራ ወደ ግብፅ ንጉሥ ቤት ከገባች ምንም ሳይቆይ፥ እግዚአብሔር በአብራም አለማመን የተፈጠረውን ስሕተት ማስተካከል ጀመረ። እግዚአብሔር ቃሉም ሆነ የተስፋ ቃል ኪዳኖቹ እንዲጠፉ አይፈቅድም (ሕዝ. 36፡22)። ለአብራም ሊያደርግለት ተስፋ የሰጣቸው ነገሮች ሊጠፉ ተቃርበው በመሰሉበት ሰዓት እግዚአብሔር በፈረኦን ላይ በመፍረድ ቤቱን በበሽታ መታው።

23ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) በይበልጥ ከኃጢአት ንጹሕ የነበረው አብራም ነው ወይስ ፈረኦን?

ለ) እግዚአብሔር አብራምን ሳይሆን፥ ፈረኦንን የቀጣው ለምን ይመስልሃል?

ፈረኦን ሦራ የአብራም ሚስት እንደሆነችና እግዚአብሔር ለኃጢአቱ እየቀጣው እንደሆነ ተረዳ። በግብፃውያን ባሕል፥ ውሸትን መናገር እንደ ትልቅ ክፋት ይቆጠር ነበር። ስለሆነም፥ አብራምን ወደ ፊቱ በጠራው ጊዜ፥ ፈረኦን ስለ መዋሸቱ ወቀሰው። ከዚያም አብራምን ከግብፅ በኃፍረት አስወጣው።

አብራምና ሦራ ከመጡበት ጊዜ ይልቅ የበለጠ ሀብት ይዘው በሰላም ከግብፅ ወጡ። ዳሩ ግን በግብፃውያን ፊት ምስክርነታቸው ተበላሽቶአል።

24ኛ ጥያቄ፤- ከዚህ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸውን የሕይወት መመሪያዎች ዘርዝር።

በእምነት ጉዞአችን ማስታወስ የሚያሻን ሦስት አስፈላጊ ነገሮች አሉ።

በመጀመሪያ፥ ነገሮችን በገዛ ሥልጣናችን ለማድረግ መሻት የለብንም። የእራሳችንን እቅዶች ስናወጣ፥ በእራሳችን ጥበብ ብቻ አንድ ነገር ለማግኘት ወይም ከአንድ ነገር ለማምለጥ ስንሻ፥ ከእግዚአብሔ ፈቃድ ውጭ በመውጣት አደጋ ላይ ወድቀናል ማለት ነው። እግዚአብሔር እኛን ለመጠበቅ፥ የእኛ ዕርዳታ አያሻውም። እራሳችንን ለመርዳት መዋሸት ትክክል አይደለም። ይህን በማድረግ፥ እምነት በማጣትና ሕይወታችንን በማጥፋት አደጋ ላይ እንወድቃለን። ለጊዜው ጥቅም ልናገኝ ብንችል እንኳ፥ በመጨረሻው ለውሳኔዎቻችንና ለሥራዎቻችን መከራ እንቀበላለን። መልካሙን ለማምጣት ክፉ መንገድ ልንጠቀም አንችልም። ይህን ማድረግ ኃጢአት በመሆኑ፥ በመጨረሻ እንሰቃይበታለን።

25ኛ ጥያቄ፤- ሀ) አንተ የምታውቃቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች ከመከራ ለማምለጥ ወይም አንድ ነገር ለማግኘት እንዴት ውሸት እንደ ተናገሩ ግለጽ።

ለ) ምን ማድረግ ነበረባቸው?

ሁለተኛ፥ ነገሮችን ለግል ጥቅማችን ብቻ ለማድረግ ስንነሣ፥ ብዙውን ጊዜ ክርስቲያናዊ ምስክርነታችንን እናጣለን።

የምንጠቀምበትም ሆነ የምንጎዳበትም ነገር ቢሆን፥ እውነቱን በመናገራችን የምንታወቅ ሰዎች ልንሆን እንደሚገባን መጠንቀቅ አለብን።

26ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) ብዙ ጊዜ እውነትን መናገር ለክርስቲያኖች አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድነው?

ለ) ታማኝ ያለ መሆን ክርስቲያናዊ ምስክርነታችንን እንዴት ይጎዳዋል?

ሦስተኛ፥ ምንም እንኳ በእራሳችን ጥበብ ወይም ባለመታዘዝ ስንመላለስ በሕይወታችን ውስጥ ብዙ ችግሮች ልንፈጥር ብንችልም፥ ይህ ማለት እግዚአብሔር ይተወናል ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ስላሉን፥ እግዚአብሔር የሰጠንን የተስፋ ቃሎቹን ለማሟላትና ስሕተቶቻችንን ለማስወገድ ይሠራል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሁል ጊዜም ለክፉ ምርጫችን እንድንሰቃይ ቢያደርገንም፥ ጥበቃውን ከእኛ አያርቅም። መጥፎ ምርጫ ስናደርግ፥ ያ ለሕይወታችን የመጨረሻው አይደለም። እግዚአብሔር ጸጋን የተሞላ አምላክ ነው። ይቅር ይለናል። አንዳንድ ጊዜም የሠራናቸውን ስሕተቶች ያስወግድልናል። ከሁሉም በላይ፥ እግዚአብሔር በገርነቱ መጥፎ ምርጫዎቻችንን ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ዕድገት በሚበጅ መልኩ ለመልካም ሊለውጥ እንደሚችል እናውቃለን (ሮሜ 8፡28 ተመልከት)።

አብራም፥ በተለይም ሚስቱን በተመለከተ፥ በሕይወቱ እግዚአብሔርን ለመታመን አስቸጋሪ ጊዜ አጋጥሞት ነበር። ከብዙ ዓመታት በኋላም ያኑን ኃጢአት ሲደግም እንመለከታለን (ዘፍ. 20)። ተመሳሳይ ኃጢአት ውስጥ ለወደቀው፥ ለልጁ ይስሐቅም ይህ አስቸጋሪ ነበር (ዘፍ. 26፡1-11)።

27ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 13ን አንብብ። ሀ) አብራም ወደ ከነዓን በተመለሰ ጊዜ የሄደው ወዴት ነበር?

ለ) ወደ ቤቴል እንደተመለሰ ወዲያውኑ ምን አደረገ?

ሐ) በአብራምና በሎጥ መካከል የተፈጠረው ችግር ምን ነበር?

መ) ይህ በመካከላቸው ትልቅ ችግር ሊያስከትል የሚችለው እንዴት ነበር?

ሠ) ጭቅጭቁን ለማብረድ አብራም ምን አደረገ?

ረ) ይህ የአብራምን እምነት ያሳየው እንዴት ነው?

ሰ) ሎጥ የት ለመስፈር መረጠ?

ሸ) የሎጥ ምርጫ ከምን አኳያ ነበር?

ቀ) እግዚአብሔር ለአብራም ምን የተስፋ ቃል ሰጠው?

ከዚህ ቀደም፥ በሥራ በኩል የሚገኘው የትውልድ የተስፋ ቃል ለአደጋ መጋለጡን ያየነውን ያህል፥ አሁን ደግሞ የከነዓንን ምድር እንደሚያወርሳቸው እግዚአብሔር የሰጣቸው የተስፋ ቃል እንዴት በአደገኛ ሁኔታ ላይ እንደ ወደቀ እንመለከታለን። ይህ አደጋ አሁንም የመጣው አብራም ካደረገው ደካማ ውሳኔ የተነሣ ነው። እግዚአብሔር አብራምን ሎጥን ከእርሱ ጋር እንዲያመጣ እንዳልነገረው ታስታውሳለህ - የአብራም ምርጫ እንጂ! በምናደርጋቸው ውሳኔዎች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻናል። እግዚአብሔርን ሳንታዘዝ ስንቀር፥ ወይም እግዚአብሔር እንዲመራን ሳንጠይቅ ስንመርጥ፥ ውሳኔዎቻችን ለረዥም ጊዜ ከችግር ላይ ሊጥሉን የሚችሉ ውጤቶች ሊያስከትሉ ይችላሉ። ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ልናገኝ ብንችልም፥ ብዙውን ጊዜ የነዚያ ውሳኔዎች ውጤቶች በቀረው ሕይወታችን ሁሉ ተጽዕኖ ያሳድሩብናል። ዛሬ አብራም ሎጥን ከእርሱ ጋር ለመውሰድ ካደረገው ምርጫ የተነሣ፥ በሁለቱ መካከል እንዴት ያለመግባባት እንደተፈጠረ እንመለከታለን።

28ኛ ጥያቄ፤ - ሀብት ለክርስቲያኖች ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግር ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

አብራም ከግብፅ እንደወጣ ወደ ከነዓን ተመለሰ። በመጀመሪያ ቤቱ ወደ ነበረችው ወደ አዜብ (ኔጌብ) ሄደ። ከዚያም፥ ቀደም ሲል ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ተገናኘበትና መሠውያ ወደ ሠራበት ወደ ቤቴል የሰሜን አቅጣጫ ይዞ ተጓዘ። በዚያም አብራም በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት አደሰ። ምናልባት እግዚአብሔርን ይቅርታ

በመጠየቅ በቀሪ ዘመኑ ለመከተል ቃል ኪዳን ገብቶ ይሆናል። ይህም ወደ ሕይወቱ መታደስ ስለ መራው፥ በእምነት ጉዞው የሚያጋጥመውን ቀጣይ መከራ ለመጋፈጥ ዝግጁ ነበር። አብራም በግብፅ እግዚአብሔርን ስለማምለኩ የሚናገር ምንም መረጃ የለም።

እግዚአብሔር አብራምን ለመባረክ የገባቸውን የተስፋ ቃሎች በታማኝነት ፈጽሞአል። አብራምና ሎጥ ሁለቱም በለጸጉ። ዳሩ ግን ይህ ብልጽግና በሁለቱ መካከል አለመግባባትን አስከተለ። ትንሽ ውኃና የግጦሽ መሬት ባለበት አካባቢ ስለ ነበሩ፥ ለከብቶቻቸው የሚሆን በቂ ውኃና ምግብ አልነበረም። ደግሞም ለከብቶቻቸው መሬት የሚሹ ከነዓናውያንም በምድሪቱ ውስጥ ነበሩ። እንስሳትን የሚጠብቁ ሰዎች እርስ በእርሳቸው መፋጀት ጀመሩ።

ሰላም ለመፍጠር በማሰብ፥ አብራም ሎጥን ለመኖር የሚፈልግበትን አካባቢ እንዲመርጥና እራሱም በሌላ አካባቢ እንዲኖር ጠየቀው። የተፈጸመውን ነገር ለመረዳት የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ ያሻናል፡-

1) እግዚአብሔር ምድሪቱን ሁሉ ለአብራም ለመስጠት እንጂ ለሎጥ ተስፋ አልሰጠም። ስለሆነም ምድሩ ሁሉ የእርሱ ስለሆነ፥ ለሎጥ ምንም መሰጠት አልነበረበትም። ሎጥ ከእርሱ ርቆ እንዲሄድ መጠየቅ ይችል ነበር።

2) አብራም የቤተሰቡ አለቃ የሆነ ታላቅ ሰው ነበር። አባት እንደ መሆኑ፥ የመጀመሪያው የምድር ምርጫ የእርሱ ነበር። ሎጥ ታናሽ እንደ መሆኑ፥ የመጀመሪያውን ምርጫ፥ ከሁሉ የተሻለውን መሬት ለአብራም መልቀቅ ነበረበት።

ዳሩ ግን አብራም ለሀብት አልተጨነቀም ነበር። ምናልባት የዚህች ዓለም ብልጽግና ጊዜያዊ ብቻ መሆኑን ተረድቶ ይሆናል። አብራም በእግዚአብሔር ወደ ተሠራች ዘላለማዊ ከተማ እየተመለከተ እንደነበር ዕብራውያን 11፡10 ይናገራል። አብራም ከጊዜያዊ የዓለም ብልጽግና ይልቅ፥ ለቤተሰብ ሰላም የበለጠ ሥፍራ ሰጥቶ ነበር። እግዚአብሔር ምድሪቱን ሊሰጠው ተስፋ የገባለትን ቃል እስኪፈጽም በትዕግሥት ለመጠበቅ ፈቃደኛ ነበር። አብራም በእምነት ተጓዘ። ዓይኖቹን

በዘላለማዊነትና በዘላለማዊ ነገሮች ላይ አደረገ። ይህም ወደ ትልቅ ሽልማት መራው።

ሎጥ በማየት ተመላለሰ። በሥጋዊ ዓይኖቹ በሚያያቸው ነገሮች ተማመነ። ዳሩ ግን በሥጋዊ ዕይታ መጓዙ፥ ወደ ታላቅ ፈተና፥ በመጨረሻም ወደ ምግባረ-ብልሹነት መርቶታል።

29ኛ ጥያቄ፥ - ሀ) አብራም በሀብት ላይ የነበረው አመለካከት ያለተለመደ ዓይነት የሆነው በምን መንገድ ነበር?

ለ) ብዙውን ጊዜ የገንዘብ ፍቅር ክርስቲያኖችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ወደ ኋላ የሚጎትታቸው እንዴት ነው?

አብራም የመጀመሪያውን የመሬት ምርጫ ለሎጥ ሰጠው። የፈለገውን የትኛውንም የመሬቱን ክፍል መውሰድ ይችል ነበር። ሎጥ ስለ አብራምና ስለ ፍላጎቱም ከመጨነቅ ይልቅ፥ የስግብግብነት እርምጃ ወሰደ። ለእራሱ የተሻለውን ብቻ ፈለገ። እንደ ሔዋን፥ ለዓይኖቹ መልካም የሆነውን መረጠ። በተራራ ጫፍ ላይ ወጥቶ በመቆም፥ አሁን ሙት ባሕር ተብሎ የሚታወቀውንና ለምለም ሸለቆዎች የሞሉበትን ሥፍራ ተመለከተ። ይህም የሰዶምና ገሞራ ክልል ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በዚያ የሚኖሩ ሰዎች «ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች» እንደ ነበሩ ይናገራል። ምናልባት ሎጥ ሰዎቹ ክፉ ስም እንዳላቸው ሊያውቅ ቢችልም፥ ዳሩ ግን ያየው ነገር አስደሰተው። ስለሆነም ከስግብግብነት ፍላጎቶች አኳያ መረጠ። ይህ ስለሚያስከትለው የወደፊት መከራ ምንም አላስተዋለም። የከነዓንን ምድር ለቅቆ ሲሄድ፥ የተስፋዪቱን ምድር መልቀቁ ነበር። የሎጥ የስግብግብነት ውሳኔ ከእግዚአብሔር ጥበቃና ለአብራም ተስፋ ከገባለት በረከቶች ለየው።

አብራም ዓኖቹን በዘላለማዊ ነገሮች ላይ በማስቀመጥ፥ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት አሳይቷል። ስለ ገንዘብ አልተጨነቀም ነበር። ይበልጥ ያተኮረው እግዚአብሔርን በማስደሰቱ ላይ ነው። ምንም እንኳ በዓለም አመለካከት፥ አብራም ሁለተኛ ደረጃ የሆነውን ምድር ቢያገኝም፥ በእግዚአብሔር ላይ ከነበረው እምነቱ የተነሣ፥ እግዚአብሔር ሸልሞታል። እግዚአብሔር አስቀድሞ ከአብራም ጋር የገባውን የተስፋ ቃል አደሰው። እግዚአብሔር

አብራምን የከነዓንን ምድር ወደ ሰሜን፥ ደቡብ፥ ምሥራቅና ምዕራብ እንዲመለከት ተናገረው። አብራም የሚመለከተውና የሚራመድበት ምድር ሁሉ፥ የትውልዶቹ ውርስ የሚሆን ነበር። እንዲሁም እግዚአብሔር ዘሮቹ እንደ ምድር አሸዋ እንደሚበዙ ለአብራም ተናግሯል። እግዚአብሔር እንዲህ ሲል፥ ለመቁጠር እስከማይቻል ድረስ እንደሚበዙ መናገሩ ነበር።

ሆኖም አብራም የከነዓንን ምድር በፍጹም አልተቀበለም ነበር። የነበረው ብቸኛው ነገር የመቃብር ቦታው ነበር። ዳሩ ግን ከ400 ዓመታት በኋላ፥ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ስላከበረ፥ በኢያሱ መሪነት እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር ወረሱ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ ሎጥ ለጊዜው የፈለገውን ተቀበለ። እጅግ ብልጽግና በበዛበት የከነዓን ምድር ክፍል ይኖር ነበር። ዳሩ ግን የነበረውና የነበረበትም አካባቢ ሁሉ በእሳት ስለወደመ፥ በመጨረሻ ባዶ እጁን ቀረ።

30ኛ ጥያቄ፤ - ብልጽግና ለክርስቲያን መሪ ወይም ለቤተ ክርስቲያን ዕንቅፋት ሲሆን ያየኸው እንዴት ነው?

ለክርስቲያን እንደ ቁሳዊ በረከቶች ለማሸነፍ የሚያስቸግር ፈተና የለም። ቁሳዊ በረከቶች የአንድን ሰው የእምነት ጉዞ የሚያደናቅፉ አራት መሰናክሎችን ያስከትላሉ። በመጀመሪያ፥ ሀብታም ሰዎች ከሁሉም በላይ ለንብረታቸው ወደ መሳሳቱ ያዘነብላሉ። ባላቸው የሀብት መጠን እስከዚህም አይረኩም። ሁል ጊዜም ተጨማሪ ይፈልጋሉ። ሁለተኛ፥ ሀብታም ሰዎች በጣም ስግብግብ ወደ መሆን ያደላሉ። ስለ ሌሎች ግድ የላቸውም። የራሳቸውን ሀብት ስለሚጠብቁበት ሁኔታ ብቻ ያሰላስላሉ። ሦስተኛ፥ ሀብታም ሰዎች ስለ ዘላለማዊ ነገሮች ዝንጉዎች ወደ መሆን ያዘነብላሉ። የአሁኑን ኑሮ ስለ መኖር አብዝተው ስለሚጨነቁ፥ በሚሞቱበት ጊዜ ዘላለማዊነት እንደሚጠብቃቸው ይዘነጋሉ። አራተኛ፥ ለሀብታም ክርስቲያኖች የእምነትን ሕይወት መኖር በጣም ከባድ ነው። በእግዚአብሔር ሳይሆን፥ በሀብታቸው ወደ መታመኑ ያደላሉ።

31ኛ ጥያቄ፤ - እነዚህን አራት ነገሮች በሀብታም ሰዎች፥ ይልቁንም በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የተመለከትካቸው እንዴት ነው?

ሀብታም መሆን ኃጢአት አይደለም። ዳሩ ግን እነዚያ እግዚአብሔር የባረካቸው ሰዎች ሀብታቸውን ስለሚመለከቱበት ሁኔታ መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል። እግዚአብሔር የሚሰጠን ሀብት ሁሉ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም እንድንጠቅምበት የተሰጠን ስጦታ ነው። ሀብቱ ከእኛ በሚወሰድበት ጊዜም፥ ኢዮብ የነበረው ዓይነት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል። ኢዮብ «እግዚአብሔር ሰጠ፥ እግዚአብሔር ነሣ፤ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን» ብሎ ነበር (ኢዮብ 1፡21)። እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርሱም በጥንቃቄ መታዘዝ ከዚህ ዓለም ብልጽግና ሁሉ በላይ አስፈላጊ ነው።

ሁላችንንም ሁለት ምርጫዎች ያጋጥሙናል - በማየት ወይም በእምነት መጓዝ እንችላለን። ሎጥ እንዳደረገው በማየት ስንጓዝ፥ በቁሳዊ ነገሮች ላይ እናተኩራለን። እነዚህም በዓይናችን ለማየት የምንችላቸው ነገሮች ናቸው። ውሳኔዎቻችንንም እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ሳይሆን፥ በራሳችን ፍላጎቶች መሠረት እንወስናለን። ምንም እንኳ ይህ ለጊዜው ሊጠቅመን ቢችልም፥ በመጨረሻ ትርጉም የሌለው ከንቱ ነገር ነው። ዳሩ ግን ልክ እንደ አብርሃም፥ በእምነት ብንጓዝ፥ ዓለምን በሥጋዊ ዓይኖቻችን ብቻ ከማየት እንታቀባለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደታየው፥ ዓለምን በእግዚአብሔር ዓይኖች አማካኝነት እንመለከታለን። እቅዶቻችንንና አሳቦቻችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር በማስገዛት፥ እርሱን ብቻ ለመታዘዝ እንፈልጋለን። ይህም ማለት ራሳችን ከመሥራት ይልቅ እግዚአብሔር እንዲሠራ በትዕግሥት መጠበቅ ማለት ነው። በምድር ላይ ሳለን ላንሸለም ብንችልም፥ ዳሩ ግን በመጨረሻ እግዚአብሔር ይሸልመናል።

32ኛ ጥያቄ፤ - አንተስ በእምነት ነው ወይስ በማየት እየተመራህ በመጓዝ ላይ ያለኸው? ለመልስህ ምክንያቶችን ስጥ።

ሦስተኛ ቀን፡ - ዘፍጥረት 14

የእምነት ጉዞ ቀላል ጉዞ አይደለም። ይልቁንም፥ እንደ ውጊያ ተደርጎ ተገልጾአል። መዋጋትና ማሸነፍ የሚያስፈልጋቸው ጦርነቶች አሉ። አብራም በጊዜው ጠላቶቹ ከነበሩት ጋር መዋጋት ነበረበት። የእስራኤል ሕዝቦች መውጋትና ማሸነፍ የሚገባቸው ከነዓናውያን ከፊት

ለፈታቸው ነበሩባቸው። ውጊያው ለክነዓናዊያን ሥጋዊ ነበር። እኛንም ውጊያ የሚጠብቀን ሲሆን፥ ውጊያችን ግን መንፈሳዊ እንጂ ሥጋዊ አይደለም።

33ኛ ጥያቄ፤- ኤፌ. 6፡10-18 አንብብ። ውጊያ የሚካሄደው ከማን ጋር ነው? የጦር ዕቃዎቻችንስ ምንድን ናቸው?

ክርስቲያን ከሚታዩ ሥጋዊ ጠላቶች ጋር እየተዋጋ አይደለም። ውጊያው የእምነት ጉዞውን ለማጥፋት ከሚፈልጉ ከስውር ነገሮች ጋር ነው። ልንዋጋቸው የሚገቡ ሦስት ታላላቅ ጠላቶች አሉን። በመጀመሪያ፥ ሰይጣንና የእርሱ ኃይሎች የሆኑ አጋንንቶች አሉ። ሊያሸንፉንና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሊያጠፉ ባለማቋረጥ ይጥራሉ። ሁለተኛ፥ ከዓለም የኑሮ ዘይቤ ጋርም እንዋጋለን። ይህን ስንል፥ የእግዚአብሔርን ነገሮች የሚቃወሙ የዓለም ሕዝቦች አመለካከቶችንና ሁኔታዎችን ማለታችን ነው። ሦስተኛ፥ ከአዳም ከወረሰነው የኃጢአት ተፈጥሮ፥ ወይም ሥጋ ጋር እንዋጋለን። ይህ የኃጢአት ተፈጥሮ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንድንሠራ ባለማቋረጥ ይታገላል። ስለዚህ እንደ አብራም የምናልፍባቸውና የምናሸንፋቸው የግል ፈተናዎች አሉን።

34ኛ ጥያቄ፤- ዘፍጥረት 14ን አንብብ። ሀ) ከነዓንን ለመውጋት የተሰበሰቡትን የአራት ነገሥታት ስም ዘርዝር።

ለ) እነርሱን ለመቋቋም የሞከሩትን የአምስት ነገሥታት ስም ዘርዝር።

ሐ) የጦርነቱ ውጤት ምን ነበር?

መ) ይህ በሚሆንበት ጊዜ ሎጥ የት ነበር?

ሠ) በሎጥ ላይ የደረሰው ነገር ምን ነበር?

ረ) አብራም ምን አደረገ?

ሰ) ከጦርነቱ በኋላ ከአብራም ጋር የተገናኙ ሁለት ነገሥታት እነማን ነበሩ?

ሸ) ለሁለቱም የአብራም ምላሽ ምን ነበር? ምላሾቹን አወዳድር።

1. በከነዓን ምድር የተደረጉ ውጊያዎች (14፡1-16)

አብራም በተለያዩ ነገሥታት መካከል ጦርነት በሚጧጧፍበት ዓለም ውስጥ ኖሯል። በእነዚያ ጊዜያት፥ አብዛኛዎቹ ነገሥታት በተወሰኑ ከተሞችና በአካባቢያቸው ላይ ይገዙ ነበር። በታላላቅ አገሮች ላይ የሚገዙ ነገሥታት አልነበሩም። የበለጠ ኃይልና አገዛዝ ለማግኘት የተለያዩ ከተሞች ነገሥታት በፌዴሬሽን (ማለት በአንድ አገዛዝ ሥር የተጠቃለሉ ናቸው።) ይዋሐዱ ነበር። ከዚያም ደካማ ነገሥታትን በመውጋት ግብር እንዲከፍሉላቸው ያስገድዱ ነበር።

ከከነነዓን በስተሰሜን አራት አበይት ነገሥታት ነበሩ። እነርሱም የሰናዖር፥ የእላሳር፥ የኤላምና የጎይም ነገሥታት ነበሩ። እነዚህ ሁሉ በመላጴጦምያ ምድር ውስጥ የሚገኙ ነገሥታት ናቸው። የአራቱ ነገሥታት መሪ ኮሎዶጎምር የተሰኘው የኤላም ንጉሥ ነበር። እርሱና ሦስቱ ነገሥታት በከነዓን ምድር ውስጥ የሚገኙትን ከተሞች ነገሥታት ለአሥራ ሁለት ዓመታት አስገብረዋል። ዳሩ ግን በአሥራ ሦስተኛው ዓመት፥ በከነዓን የሚገኙ ነገሥታት ለማመፅና ግብር ላለመክፈል ወሰኑ። ከዚህም የተነሣ፥ በአሥራ አራተኛው ዓመት፥ አራቱ ነገሥታት ከከነዓናውያን ጋር ለመዋጋት ከመስጴጦሚያ ገስግሰው መጡ። በዚህም ውጊያ አሸንፈው ዳግም ይገዙዋቸው ጀመር። በከነዓንና አከባቢዋ የሚገኙትን ነገሥታት ሁሉ በፍጥነት አሸንፋዋቸው። ወደ ደቡብ የከነዓን ክልል በመጡ ጊዜ፥ ከአምስት ከተሞች ማለትም ከሰዶም፥ ከገሞራ፥ ከአዳማ፥ ከሰቦይና ከዞዓር ከመጡ ሠራዊት ጋር ተገናኙ። የእነዚህ ወታደሮች መሪዎች የከተሞቹ ነገሥታት ነበሩ። እነዚህ አምስት ነገሥታት በፍጥነት ተሸነፉና በከተሞቻቸው ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በምርኮኛነት ተወሰዱ።

ቀደም ሲል፥ ሎጥ በሰዶም ከተማ አጠገብ በሚገኙ ሜዳማ ሥፍራዎች በድንኳን ውስጥ እንደሚኖር የተመለከትን ሲሆን፥ በዘፍጥረት 14 ደግሞ በከተማይቱ ውስጥ ስለ መኖሩ እናነባለን። ቀስ

በቀስ በዚያች ኃጢአተኛ ከተማ ሕይወት እየተሳበ ነበር። በዚህ ጊዜ በከተማይቱ ውስጥ ስለ ነበረ ተማርኮ ሂዶአል ማለት ነው።

35ኛ ጥያቄ፤ ይህ በኃጢአት ከሚወድቅ ክርስቲያን ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

አብራም የሰዶምን ውድቀትና የወንድሙን ልጅ መማረክ የሚያበስረውን ዜና በሰማ ጊዜ፥ ለጦርነት ተዘጋጀ። አብራም በአሞራዊ መምሬ የአድባር ዛፍ አካባቢ ይኖር ነበር። «ዕብራዊ»ም ይባል ነበር። «ዕብራዊ» የሚለው ቃል ሲጠቀስ ይህ የመጀመሪያ ጊዜው ነው። በዚህ ዓይነት፥ ጸሐፊው እስራኤላውያን እንደ ነገድ ወይም ጎሳ ይቆጠሩ እንደ ነበር ያሳያል። አብራም እንደ ነገድ አለቃ ታይቷል።

የጎሳ አለቃ እንደ መሆኑ፥ አብራም በሕብረተሰቡ መካከል ከሚኖሩት ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል። በቃል ኪዳኑ ውስጥ በሰላም አብሮ ለመኖርና ከቃል ኪዳኑ ተጋቢዎችም መካከል አንዱ ወደ ጦርነት ሲሄድ አብረው ለመዋጋት የተስማሙባቸው ነጥቦች እንደሚኖሩ አንጠራጠርም። ለዚህ ነው አብራም ከመስጴጦሚያ ነገሥታት ጋር ለመዋጋት 318 የሰለጠኑ ሰዎችን ከጎሳው ሲወስድ፥ የአውና፥ የኤሽኮልና የመምሬ ነገሥታት ዕርዳታ የደረሰለት (ዘፍ. 14፡24 ተመልከት)። ከዚህ ውስጥ የአብራም ማህበረሰብ ምን ያህል እንዳደገና በዙሪያው በሚኖሩት አሕዛቦች ምን ያህል የተከበረ እንደ ነበር ለመመልከት እንችላለን።

በአንጻራዊ አመለካከት አነስተኛ የነበረውን ተዋጊ ኃይሉን በመያዝ፥ አብራም ነገሥታቱን በመስጴጦሚያ ውስጥ አሳደዳቸው። በእኩለ-ሌሊት፥ መታቸውና እስከ ሶርያ ደማስቆ ድረስ እንኳ በመጓዝ ወደ ሰሜኑ ዳርቻ አባረራቸው። ምንም እንኳ አነስተኛ ኃይል ቢሆንም፥ እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ ድልን ሰጠው።

ይህ ብዙም ሳይቆይ ከከነዓናውያን ጋር ለሚዋጉ እስራኤላውያን ትምህርት ሆኗቸው ነበር። ምን ጊዜም እስራኤላውያን የቁጥር ብልጫ አይኖራቸውም። ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚተማመኑት በቁጥራቸው ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጎን ቆሞ በመዋጋቱ እውነታ ላይ ነው። እግዚአብሔር ከጎናቸው ስላለ ያሸንፋሉ።

36ኛ ጥያቄ፤ በመነፈሳዊ ጦርነት ውስጥ በምንኖርበት ጊዜ፥ ይህ የሚያበረታታን እንዴት ነው?

2. የአብራም ከሰዶምና ከኢየሩሳሌም ነገሥታት ጋር መገናኘት (14፡13-24)።

ብዙውን ጊዜ መሪዎች በኃጢአት ወደ መውደቅ የሚያጋድሉት በድል ወቅት ነው። በትዕቢት ተይዘው በእግዚአብሔር ላይ መደገፋቸውን ያቆሙና ይወድቃሉ። ይህ ፈተና አብራም ሁለቱን ነገሥታት ባገኘበት ታሪክ ውስጥ ተስተውሏል።

የመጀመሪያው ንጉሥ የሰዶም ንጉሥ ነበር። በአራቱ የመስጴጦሚያ ነገሥታት ተሸንፎ፥ ወደ በረሃ ለመሸሽ ተገድዶ ነበር። ከተማዋም ተበዝብዛ ነበር። አብራም ከሰዶም ከተማ ምርኮ ያስመለሳቸውን ንብረቶች ይዞ ከጦርነት መመለሱን በመስማት፥ ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ወደ ሰሜን በብዙ ኪሎ ሜትር የሚቆጠር ርቀት ተጓዘ። በጊዜው ሳሌም ትባል ከነበረችው ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ ተገናኙ።

ሁለቱ ነገሥታት በተገናኙ ጊዜ፥ የሳሌም ንጉሥ የተባለው ሌላ ንጉሥ ሊገናኛቸው መጣ። እነ አብራም ረኀቡ ርቀት ከመጓዛቸው የተነሣ የዛለውን ጉልበታቸውን ለማጽናት ምግብ እንዲበሉ የሳሌሙ ንጉስ አቀረበላቸው። በአብራም ዘመን እንደ ነበሩቱ በርካታ ገዢዎች ሁሉ፥ ይህም የሳሌም ንጉሥ ካህንና ንጉሥ በመሆን ጣምራ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ምንም እንኳ ዝርያው ባዕድ አምልኮ ከሚያካሂዱት አሕዛብ ቢሆንም፥ መልከ ጼዴቅ ግን እውነተኛውን አምላክ የሚያመልክ ነበረ። «እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ» ተብሏል (14፡18)።

ሙሴ በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር የተሰጠውን ሌላ ስም ያስተዋውቀናል - ኤል ኤልዮን (14፡19)። ይህ በፍጥረታት፥ በሰማይና በምድር ሁሉ ላይ የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ሥልጣን ለማመልከት የቆመ ስም ነበር።

መልከ ጼዴቅ ካህን ስለ ነበረ፥ አብራምን ባረከው። አብራምም በበኩሉ ከጦርነቱ ካገኘው ምርኮ አሥራት ሰጠው።

ምንም እንኳ ይህ ታሪክ አላስፈላጊ ቢመስልም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ውስጥ ግን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል [መዝ. (110)፡4፤ ዕብ. 5-7]። የዕብራውያን መልዕክት፥ የሳሌም ንጉሥ የሆነውን የመልከ ጼዴቅ ሕይወት፥ የሊቀ ካህኑ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት አድርጎ ያቀርበዋል። ልክ መልከ ጼዴቅ የሚለው ስም «የጽድቅ ንጉሥ» ማለት እንደሆነ ሁሉ፥ ኢየሱስም እንዲሁ የጽድቅ ንጉሥ ነው። እንዲሁም መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥ፥ ማለትም የሰላም ንጉሥ እንደ ነበረ ሁሉ፥ ኢየሱስም የሰላም ንጉሥ ነው። መልከ ጼዴቅ ካህንና ንጉሥ እንደ ነበረ ሁሉ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም ካህንና ንጉሥ ነው። በመጨረሻም፥ ልክ የመልከ ጼዴቅ አብራምን መባረክና ከእርሱም አሥራት መቀበሉ የትልቅነቱ ምልክት እንደሆነ ሁሉ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም የአብራም ልጆች ከነበሩት ከሌዋውያን ይበልጣል።

አብራምም፥ መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ወኪል መሆኑን በመረዳት፥ በረከቶቹን ተቀበለ።

ዳሩ ግን፥ የሰዶም ንጉሥ ለሆነው ሁለተኛው ንጉሥ አብራም የነበረው አመለካከት በጣም የተለየ ነበር። አብራም ሕዝቡን ስላስመለሰለት፥ የሰዶም ንጉሥ በጣም በምስጋና ተሞልቶ ነበር። ስለሆነም ለአብራም ስለ ውለታው ካሳ ሊከፍለው ፈለገ። አብራም ምርኮኞቹን ብቻ እንዲመልስለትና በተረፈ ግን ከሰዶም ምድር በብዝበዛ መልክ የያዛቸውን ንብረቶች እንዲወስድ ጠየቀው። ላይ ላዩን ሲመለከቱት፥ ይህ የለጋስነት ስጦታ ይመስላል። አብራም ጦርነት ስለተዋጋ፥ እነዚህ ንብረቶች እንደ ደመወዙ ሊቆጠሩ ይችል ይሆናል። ዳሩ ግን አብራም ምንም ነገር ለመቀበል አልፈለገም።

37ኛ ጥያቄ፤ ሀ) አብራም ከምርኮ የተገኙትን ነገሮች ለመቀበል እምቢ ያለው ለምን ይመስልሃል?

ለ) በዛሬውም ዓለም አንድ መሪ ሊጋፈጠው የሚችለውን ተመሳሳይ ፈተና ዘርዝር።

አብራም የሰዶም ንጉሥ ምን ዓይነት ሰው እንደ ነበር ተረድቷል። እግዚአብሔርን የማይፈራ፥ የኃጢአተኛ ሕዝብ ንጉሥ ነበር። አብራም ምርኮዎቹን ተቀብሎ ቢሆን ኖሮ፥ ሌሎች ሰዎች ከክፉ ንጉሥ ጋር

ኃይሉን ያስተባበረ ይመስላቸውና አብራም ኃጢአታቸውን እየደገፈ እንዳለ አድርገው እንደሚያስቡ ያውቅ ነበር። አብራም ምስክርነቱን ለመጠበቅ ይጠነቀቅ ነበር። ሀብት ለማግኘት ኃይልን እንደተጠቀመ ሰው ሆኖ ሊታወቅ አልፈለገም ነበር። ሀብቱን ከሌሎች በምስጋና መልክ ከቀረበለት ገጸ-በረከት የተነሣ እንዳገኘ መስሎ እንዲታይም አልፈለገም። ማንኛውም ሀብት ቢኖረው የሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ሰዎች ሁሉ እንዲገነዘቡ ፈለገ። ለሰዶሙ ንጉሥ በሰጠው መልስ፥ ከጦርነቱ ምርኮ ምንም ላለመውሰድ ቃል እንደገባ ነገረው። ለሰዎቹ የሕይወት ማቆያ የሚያስፈልገውን ብቻ ከተጠቀመ በኋላ፥ ከእርሱ ጋር የተዋጉት ሌሎች ሰዎች ከምርኮው ንብረቶች እንዲቀበሉ ፈቀደላቸው። በግሉ ግን ምንም ነገር አልወሰደም።

ሰይጣን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ወይ የሌሎች ክርስቲያኖችን መልካም ስም ለማጥፋት በሚያደርገው ሙከራ በጣም ጎበዝ ነው። እግዚአብሔር ድል ሲሰጣቸውና በኃይል ሲጠቀምባቸው፥ በዚህ ጊዜ ከሁሉም በላይ ለጥቃት ይፈልጋቸዋል። ብዙውን ጊዜ እነርሱን ለማጥፋት ገንዘብን ይጠቀማል። ይህ ከሚከተሉት ሁለት መንገዶች በአንደኛው መንገድ ሊፈጸም ይችላል። መሪው እግዚአብሔርን ከማገልገል ይልቅ በገንዘብ ላይ በይበልጥ እንዲያተኩር ማድረግ ይችላል። ይህም አንዳንድ ጊዜ ክፍያቸው ወይም ጥቅማቸው በቂ ካልሆነ ለመሥራት በማይፈልጉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ታይቷል። ወይም፥ ሰይጣን መሪው ወንጌልን በመስበክ ብልጽግናን እያካበተ እንዳለ እንዲመስለው ያደርጋል። ምንም እንኳን መሪው ንጹሕ ልብ ሊኖረው ቢችልም፥ ሌሎችን ለምን እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል እንዲጠይቁ በማነሳሳት፥ ሰይጣን የመሪውን ምስክርነትና አገልግሎት ሊያበላሽ ይችላል።

38ኛ ጥያቄ፤ ሀ) እነዚህ ሁለት ነገሮች በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ውስጥ ሲፈጸሙ አይተሃልን? የተፈጸመው ነገር ምን እንደ ነበረ ግለጽ።

ለ) እነዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በምን መንገድ እንደ አብራም ለመመለስ ይችሉ ነበር?

አስተዋዩ መሪ፥ ገንዘብ-ነክ የሆኑ ጉዳዮችን እንዴት እንደሚቀርብ ማወቅ አለበት። ሁል ጊዜም የሚከፈለው ደመወዝ ምንም ይሁን ምን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነትና የአገልግሎት ጥሪውን ከሁሉ ማስቀደም አለበት። ባለ ጸጋ ቢሆንና ዳሩ ግን ምስክርነቱን ቢያጣ ምን ዋጋ አለው?

39ኛ ጥያቄ፤ 1ኛ ቆሮ. 9፡1-18፤ 2ኛ ቆሮ. 11፡7-12 አንብብ። ሀ) ጳውሎስ የተወቀሰበት ነገር ምንድነ ነበር?

ለ) ጳውሎስ ለማድረግ እምቢ ያለው ነገር ምን ነበር? ለምን?

ታላቅ መሪ፥ መልካም ምስክርነቱን፥ በተለይም በገንዘብ-ነክ ነገሮች ለመጠበቅ፥ የበለጠ ጠንቃቃ መሆን አለበት። ለዚህ ነው ትልቅ ሐዋርያ የነበረውና ለእገልግሎቱ ገንዘብ መቀበል ይችል የነበረው ጳውሎስ፥ ከፍያ ለመቀበል እምቢ ያለው። ማንም ሰው ገንዘብ ለማግኘት ብሎ ብቻ እንደሚሠራ አድርጎ እንዲቆጥረው አልፈለገም ነበር።

40ኛ ጥያቄ፤ የንዋይ ጉዳዮችን በተመለከተ፥ ከሕይወትህ ጋር የምታዛምዳቸውን አንዳንድ ትምህርቶች ዘርዝር።

አራተኛ ቀን ዘፍጥረት 15

በእምነት ጉዞ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖችን የሚያሰናክሉዋቸው ነገሮች ይጋረጡባቸዋል። ሐዘንና ዳተኛነትም ያጋጥማቸዋል። እንግዲህ ክርስቲያን ማድረግ የሚገባው ምንድነው? እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠራለት በትዕግሥት መጠበቅ አለበት። በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች መተማመን አለበት። በዘፍጥረት 15 ውስጥ እግዚአብሔር አብራምን ማስተማር የነበረበት ትምህርት ይህንኑ ነበር።

41ኛ ጥያቄ፤ ዘፍጥረት 15ን አንብብ። ሀ) በቁጥር 1 ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል ምንድነው? ያስ ምን ማለት ነበር?

ለ) አብራም በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመረመበት ነገር ምንድን ነበር?

ሐ) የአብራም ትውልዶች ከምን ጋር ተወዳደሩ?

መ) አብራም ባመነ ጊዜ እግዚአብሔር ምን አደረገለት?

ሠ) እግዚአብሔር አብራም እንስሳቱን ምን እንዲያደርጋቸው ነገረው?

ረ) እግዚአብሔር ለአብራም የነገረው ትንቢት ምንድነው?

ሰ) እግዚአብሔር ምድሪቱን ለአብራም ወዲይውኑ እንደማይሰጠው የተናገረው ለምንድነው?

ሸ) ለአብራም የተሰጠችው ምድር ድንበሮች የትኞቹ ነበሩ?

አብራም በመጀመሪያ ሐራንን ለቆ ወደ ከነዓን ከተጓዘ ብዙ ዓመታት አልፈዋል። ቢሆንም የቤተሰብ ሐረጉን ለመቀጠል እግዚአብሔር ለአብራም ልጅ እንደሚሰጠው የገባውን የተስፋ ቃል እንደሚፈጽምለት የሚያሳይ ምልክት አልነበረም። በዚህም አብራም ተስፋ ቆረጠ። ስለሆነም እግዚአብሔር ከጸጋው ብዛት የተነሣ፥ ወደ አብራም በመምጣት፥ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ላይ ባለው እምነት እንዲጸና በሁለት መንገዶች አበረታታው።

1. እግዚአብሔር አብራምን በተናገረው ቃል አጽናናው (15፡1-6)።

አብራም ከመስጴጦሚያ ነገሥታት ጋር በመዋጋት እምነቱን ካሳየ በኋላ፥ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰጠው ሁለት አበይት የተስፋ ቃሎች በድጋሚ ለማረጋገጥ ተከታታይ ራእዮችን ይሰጠዋል። በመጀመሪያው ራእይ፥ የተስፋውን ቃል የሚወርስ ልጅ፥ ከአብራም አብራክ እንደሚወጣ አረጋገጠለት።

እግዚአብሔር ወደ አብራም በመጣ ጊዜ፥ እራሱን በሁለት መንገዶች ገልጾለታል። በመጀመሪያ እርሱ የአብራም ‹ጋሻ› ነበር። ይህን ሲል፥ እርሱ የአብራም ጠባቂ መሆኑን መግለጹ ነበር። ሁለተኛ፥ እርሱ የአብራም ‹ሽልማት› ነበር። እግዚአብሔር የአብራምን መሻቶች ሁሉ እንደሚያሟላ ተስፋ ሰጥቷል። ዳሩ ግን አብራም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነት ከሁሉ የላቀ ሽልማቱና ዋጋው መሆን ነበረበት። በቁሳዊ ሀብት አብራም ባለ ጸጋ ነበር። ይህ ግን ለእርሱ ቅድሚያ

የሚሰጠው ጉዳይ አልነበረም። ከፍተኛ ክብር የሚሰማው ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ያለው ሰው በመሆኑ ነው።

42ኛ ጥያቄ፤ እግዚአብሔርን ማወቅ ከሁሉም የሚበልጥ ሽልማታችን መሆን ያለበት በምን መንገድ ነው?

ምንም እንኳ አብራም የእምነት ሰው ቢሆንም፥ ይህ ማለት ግን የተጠራጠረባቸው ጊዜያት አልነበሩም ማለት አይደለም። እርሱ የፈለገው ሽልማት ልጅ ማግኘት ነበር። የሚያወርሰው ልጅ ከሌለው፥ ሥጋዊ በረከቶችን ማግኘት ምን ይጠቅመዋል? እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጠው ለብዙ ዓመታት ጠብቋል። ይሁንና እግዚአብሔር እንደሚሠራ የሚያሳይ ምልክት ካለመኖሩም በላይ፥ በየዓመቱ እርሱና ሦራ እያረጁ ስለሄዱ፥ ልጅ የማግኘቱ ተስፋ እየጨለመ መጣ። ሎጥ አሁን ከአብራም ጋር ባለመኖሩ፥ የቀረው ወራሽ ቢኖር ዔሊዔዘር የተባለ የደማስቆ ሰው ነበር።

ይህ በአብራም ዘመን የነበረውን ባሕላዊ ልምምድ ያንጸባርቃል። አንድ ሰው ንብረቱን የሚወርስ ልጅ ከሌለው፥ አንድም ወራሽ የሚሆን የማደጎ ልጅ ይፈለጋል፤ አሊያም ከባሪያዎቹ አንዱ እንዲወርስ ይደረጋል። ዔሊዔዘር ከአብራም ባሪያዎች አንዱና ንብረቱን ለመውረስ የታጨ ሰው ነበር። ልጅ ከተወለደ፥ ባሪያ ወራሽ ሊሆን አይችልም።

የእግዚአብሔር ምላሽ ግልጽ ነበር። አብራም ልጅ እንደሚኖረው እግዚአብሔር ተስፋ ገብቶለታል። ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር የአብራምን ትውልድ ከምድር አሸዋ ጋር ሲያነጻጽር፥ አሁን ደግሞ ከሰማይ ከዋክብት ጋር አወዳደራቸው። ለቁጥር የሚያዳግቱ መሆን ነበረባቸው። ይህ ከፍጻሜ በመድረሱ፥ ሙሴ ዘፍጥረትን በጻፈበት ዘመን ከአንድ ሚሊዮን የሚበልጡ የአብራም ትውልዶች ነበሩ። ሥጋዊ አይሁዶች ብቻ ሳይሆኑ፥ ክርስቲያኖችም የአብራም ትውልዶች በመሆናቸው፥ የዚህ ተስፋ ቃል ፍጻሜ አካል ናቸው።

43ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ሰው በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ጻድቅ የሚሆነው እንዴት ነው?

ለ) ምን ማድረግ አለበት? መልስህን ለማብራራት ጥቂት ጥቅሶችን አስፍር።

44ኛ ጥያቄ፤ «እምነት» እና «ጽድቅ» ለሚሉ ቃላት ፍቺያቸውን ጻፍ።

ዘፍጥረት 15፡6 «አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፥ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» ይላል። ይህ በዘፍጥረት፥ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቁልፍ ጥቅስ ነው። እውነተኛ ጽድቅ የሚገኝበትን መሠረት ያሳያል። በርካታ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ የምንሆነው አንድ ነገር በመሥራት እንደሆነ ያስባሉ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢሄዱ፥ ወይም በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ቢወለዱ፥ ወይም አንድ ትልቅ ነገር ለእግዚአብሔር ቢሠሩ፥ ጽድቅን በሽልማት መልክ ከእግዚአብሔ እጅ እንደሚቀበሉ ያስባሉ። በቂ ደጋግ ሥራዎችን ከሠሩ፥ ወደ መንግሥተ-ሰማያት እንደሚገቡ ተስፋ ያደርጋሉ። ዳሩ ግን ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ትክክለኛ ግንኙነት የሚመጣበት ብቸኛ መሠረት በእምነት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያሳያል።

45ኛ ጥያቄ፤ ዛሬ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘትና ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት የሚያደርጉዋቸውን አንዳንድ ነገሮች ዘርዝር።

ከዘፍጥረት 15፡6 ስለ እምነት የሚከተሉትን ነገሮች ለማየት እንችላለን። በመጀመሪያ፥ እምነት በትክክለኛ ነገር ላይ ሊጣል ይገባል። የአብራም እምነት በእግዚአብሔርና በተስፋው ቃል ላይ ነበር። አብራም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች በመስማት በእርግጠኛነታቸው ታመነ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁል ጊዜም የሚያድን እምነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ውስጥ ነው።

ሁለተኛ፥ እምነት ሁል ጊዜም የግል ነው - አይወረስም። አብራም በግሉ ማመን ነበረበት። እንደዚሁም፥ ለመዳን እያንዳንዱ ክርስቲያን በግሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን አለበት።

ሦስተኛ፥ እምነት የምናውቀውን ነገር በተግባር እንድንተረጎመው ይጠይቃል። እምነት እውነትን ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ ያወቁትን እውነት በተግባር ማዋልም ነው። አብራም ካራንን በመልቀቅ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት ከማረጋጠጡም ሌላ በተስፋ ቃሎቹም

አምኖአል። እንደዚሁም፥ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት አስገዝተን መኖር ማለት ነው።

46ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በግልህ በኢየሱስ ክርስቶስ የታመንኸው መቼ ነው?

ለ) በየዕለቱ ኑሮህ ውስጥ እምነትህ የሚረጋገጥባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

ሁለተኛው አብይ ቃል «ጽድቅ» ነው። ይህ ማለት አብራም እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ከሚፈልገው ደረጃ ላይ ደርሷል ማለት ነው። እግዚአብሔር ከሚፈልግብን ደረጃ ለመድረስ በቂ ነገሮችን ለመሥራት የምንችልበት መንገድ የለም። የእግዚአብሔር ደረጃ ፍጹም ቅድስና ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱሳን እንድንሆን ተነግሮናል (ዘሌ. 11:44)። ሆኖም ያንን ቅድስና ሊጨብጥ የሚችል አንድም ሰው አይኖርም።

ዳሩ ግን አብራም በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት እንዴት ጻድቅ ለመሆን በቃ? ባደረገው አንድ ነገር ነውን? አይደለም፤ እንዲያው ለአብራም ተሰጠው እንጂ! መጽሐፍ ቅዱስ እንደ «ተቆጠረለት» ይናገራል። አብራም የእግዚአብሔርን ቃል ተአማኒነት እንዳለው አድርጎ ስለ ተቀበለና ከተግባር ስላዋለው፥ እግዚአብሔር አብራም በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኘ አወጀ። እግዚአብሔር የሚፈልገው ጽድቅ ወደ መታዘዝ የሚመራና በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ እምነት ነው። እምነታችንንም ከተመለከተ በኋላ፥ እግዚአብሔር ጻድቅ ብሎ ይጠራናል።

47ኛ ጥያቄ፤ ሮሜ 4:3፥ 9፥18-24 እና ገላ. 3:6 ተመልከት። እኛ ሁላችን ከዳንንበት ሁኔታ ጋር ይህ የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

ይህ ጥቅስ፥ አብራም ባጠቃላይ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ጻድቅ የሆነው በዚህ ጊዜ እንደሆነ አይናገርም። አብራም ካራንን በመልቀቅ ቀደም ብሎ እምነቱን አረጋግጧል። ዘፍ. 12፥ በአብራም ጠቅላላ ሕይወት ላይ የተሰጠ የማጠቃለያ አስተያየትና በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት እንዴት ተቀባይነት እንዳገኘ የሚያሳይ ጥቅስ ነው።

2. ከአብራም ጋር የተገባው ቃል ኪዳን መታተም (15:7-21)

ከአብራም ጋር በተገባው ቃል ኪዳን ውስጥ ሁለተኛው አብይ ነገር፥ የከነዓንን ምድር በተመለከተ የተሰጠው ተስፋ ነበር። የከነዓንን ምድር በተመለከተ እግዚአብሔር ለአብራም የገባውን የተስፋ ቃል ሲያድስ፥ በአብራም አእምሮ ውስጥ አዳዲስ ጥያቄዎች መፈጠር ጀመሩ። እንዴት አድርጎ ምድሪቱን እንደሚወርስ ብዙ ለማወቅ ፈለገ።

የአብራምን ጥያቄ ለመመለስ፥ እርሱ በነበረበት ዘመን ባሕላዊ ልምድ በመጠቀም እግዚአብሔር እንደገና አረጋገጠለት። ሁለት ሰዎች እርስ በእርሳቸው ቃል ኪዳን ለመግባት ሲፈልጉ፥ ከሁሉም በላይ ማረጋገጫው መንገድ፥ አንድ እንስሳ በማረድ ቆራርጠው በሁለት ወገን ከመደቡት በኋላ፥ እያንዳንዱ ቃል ኪዳን ተጋቢ በተከፈሉት የእንስሳው ክፍሎች መካከል መራመድ ነበር። ይህንንም ሲያደርጉ፥ «እኔም በቃል ኪዳኑ ውስጥ ያሉትን ግዴታዎች ባላሟላ ለሁለት ተቆርጬ ልጥፋ» ማለታቸው ነበር። ይህ የመጨረሻው ከባድ መሀላ ነበር። እግዚአብሔር ይህንን የቃል ኪዳን ምሳሌ የሰጠው እርሱ ስላስፈለገው ሳይሆን፥ የቃል ኪዳኑ መፈጸም አሌ የማይባል እንደሆነ ለአብራም ለማረጋገጥ ነበር።

48ኛ ጥያቄ፤ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን እርግጠኝነት ለማረጋገጥ አብራም በሚያውቀው ልማድ የተጠቀመው ለምን ይመስልሃል?

ይህን ቃል ኪዳን ለመፈጸም በመዘጋጀት፥ እግዚአብሔር አብራም የተወሰኑ እንስሳትን እንዲያሰናዳ አዘዘው። እንስሳቱም ታርደውና ለሁለት ወገን ተከፍለው በመሬት ላይ ተቀመጡ። አብራም ቀኑን በሙሉ ጠበቀ። አሞራዎች ሥጋውን ለመብላት ቢወርዱም፥ አብራም አባረራቸው። እነዚህ ለመብላት የወረዱት አሞሮች ለአብራም አንድ ክፉ ነገር የሚያመለክቱ ይሆናሉ። ብዙውን ጊዜ በብሉይ ኪዳን፥ ባዕዳን ሕዝቦች በአሞሮች ተመስለዋል (ሕዝ. 17፡3፥7)።

ቀኑ በምሽት ሲተካ፥ እግዚአብሔር ለአብራም ሁለተኛውን ራእይ ሰጠው። በራእዩም ውስጥ፥ እግዚአብሔር በምድጃ ጢስና በእሳት ነበልባል አምሳል ለአብራም ተገለጸለት። ጢስና እሳት ሁለቱም የእግዚአብሔርን ሕልውና የሚያመለክቱ ነበሩ (ዝፀ. 19 ተመልከት)። ቅድስናውንና ንጽሕናውን ያንጸባርቃሉ። ከዚያም እግዚአብሔር

ከአብራም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በማተም፥ በተከፈሉት ሥጋዎች መካከል ተራምዶ አለፈ።

በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የወደፊት ዕጣ ለአብራም ነገረው። በባዕድ አገር ለ400 ዓመታት በባርነት እንደሚገዙ ነገረው። ከዚያም በባርነት የገዛቸውን አገር እግዚአብሔር እንደሚቀጣውና በብዙ ብልጽግና እንደሚመለሱ አስታወቀው። የአብራም ትውልዶች የከነዓንን ምድር የሚወርሱት በዚያን ጊዜ ብቻ ነበር።

49ኛ ጥያቄ፤ ይህ ትንቢት የተፈጸመው እንዴት ነበር?

ሙሴ መጽሐፉን በጻፈ ጊዜ፥ ይህ ትንቢት በመፈጸም ሂደት ውስጥ ነበር። እስራኤላውያን በግብፅ በባርነት ሥር ሲሆኑ፥ አሁን ግን እግዚአብሔር እነርሱን ለማስለቀቅ እየሠራ ነበር። በዘመናቸው የእግዚአብሔርን እጅ በሥራ ላይ ማየት ነበረባቸው።

አብራም በትንቢቱ ቃል ሳይደነግጥ አይቀርም። እግዚአብሔር ምድሪቱን እንደሚያወርሰው የተስፋ ቃል ሰጥቶት ነበር። ይሁን እንጂ፥ አሁን ይህ እስኪፈጸም ድረስ የ400 ዓመታት ጊዜ እንደሚፈጅ እግዚአብሔር እየተናገረው ነበር።

ይህ ትንቢት በዚህ ወቅት የተነገረው ለምንድነው? ሁለት ምክንያቶች አሉ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ወደፊት የሚፈጸሙትን ነገሮች እንደሚቆጣጠር ለአብራም ለማሳየት ስለፈለገ ነው። እግዚአብሔር የአብራምን ትውልድ በጥንቃቄ ይጠብቃቸዋል። ምንም እንኳ በአስቸጋሪ ጊዜያት ውስጥ ሊያልፉ ቢችሉም፥ ፍጻሜውን እርሱ ይቆጣጠረዋል። እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ላይ ስለሆነ፥ የተስፋዱቱን ቃል የመውረሳቸው እውነታ የተረጋገጠ ነበር።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር መከራቸውን አስቀድሞ እንደተመለከተና ፍጻሜውንም እንደሚያውቅ፥ ሙሴ ለእስራኤላውያን ለማሳየት ስለፈለገ ነው። የዘፍጥረት መጽሐፍ የተጻፈው፥ ወይ ከዘጸአት ጥቂት ቀደም ብሎ፥ አሊያም ልክ ከዘጸአት ቀጥሎ ነበር። ወደ ኋላ ተመልሰው እስከ አብራም ዘመን ድረስ 400 ዓመታት በመቁጠር እግዚአብሔር ለአብራም የገባቸው የተስፋ ቃሎች በእነርሱ እንደሚፈጸሙ ለማወቅ

ይችሉ ነበር። ጠላታቸው ግብፅ መሸነፍ ነበረባት። ስለሆነም ሊበረታቱ፥ በእግዚአብሔር ላይ እምነት ሊኖራቸውና ምድሪቱን ለመውረስ ወደ ፊት ሊገሰግሱ ይገባቸው ነበር።

እግዚአብሔር አብራም ለምን ምድሪቱን አሁኑኑ እንደማይወርስ ምክንያት ሰጥቷል። እግዚአብሔር «የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና» ብሏል። አሁንም የእግዚአብሔርን ምህረት እናያለን። ከዚህ ቀደም በጥፋት ውኃ ጊዜ ሕዝብ ንስሐ እንዲገባ ለ 120 ዓመታት በትዕግሥት እንደጠበቀ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ፥ ከነዓናውያን (እዚህ ጋ አሞራውያን የተባሉት) ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ 400 ዓመታት ጠብቋል። ሆኖም እንደ ጥፋት ውኃ ዘመን ሰዎች ሁሉ፥ እነዚህም ንስሐ ባለመጋብታቸው በእስራኤላውያን ተደመሰሱ። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር በከነዓናውያን ላይ ለምን እንደፈረደና ለምን እስራኤላውያን እንዲያጠፉዋቸው እንዳዘዘ ያሳየናል። እስራኤላውያን እነርሱን ስለ ኃጢአታቸው በመቅጣት የእግዚአብሔር መሳሪያዎች ነበሩ።

50ኛ ጥያቄ፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡3-9 አንብብ። የኢየሱስ መዘግየት በተመሳሳይ ምክንያት መሆኑ እንዴት ነው?

በማጠቃለያ፥ እግዚአብሔር ለአብራም ማረጋገጫ ሰጥቶታል። ይህንንም በሁለት መንገዶች አድርጓል። በመጀመሪያ፥ ሕይወቱ ሰላማዊ እንደሚሆንንና ዕድሜውም እንደሚረዝም አረጋግጦአል። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን እውነተኛነት አብራም ሊረዳ በሚችልበት መንገድ አሳይቷል።

ከዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ልናጤናቸው የሚገቡ ሁለት አስፈላጊ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ለአብራም ዘሮች የሚሆነውን የከነዓን ዳርቻ ወስኖአል። የደቡብ ዳርቻ «የግብፅ ወንዝ» ይሆናል። ይህ የሚያመለክተው ወደ አባይ ወንዝ ሳይሆን፥ በሲና ምድር ከልል ወደሚገኘው ወንዝ ነው። (ካርታውን ተመልከት)። የሰሜኑ ዳርቻ ታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ. ነበር። በታሪክ፥ እስራኤል በዳዊትና በሰሎሞን የአገዛዝ ዘመናት ብቻ እነዚህ ዳርቻዎች ነበሯት። ስለሆነም ብዙ ሊቃውንት ኢየሱስ በምድር ላይ በሚገዛበት ዘመን የእስራኤል ዳርቻ

የሚሆነው ይህ ሥፍራ እንደሆነ ያስባሉ። እንዲሁም እግዚአብሔር በከነዓን ይኖሩ የነበሩትን የከነዓን ነገዶች ስም ሲጠቅስ፥ እነርሱም ከምድራቸው ሊፈናቀሉና ምድራቸውም ለእስራኤላውያን ትሰጥ ነበር።

ሁለተኛ፥ በተከፈሉት ሥጋዎች መካከል እግዚአብሔር ብቻ እንጂ፥ አብራም እንዳላለፈ ልብ ማለት አለብን። ይህም ማለት አብራም የተስፋ ቃሉን ለማግኘት ማሟላት የሚያስፈልገው ቅድመ-ሁኔታ አልነበረም ማለት ነው። ያለ ምንም ግዴታ እግዚአብሔር የገባለት ቃል ኪዳን ነበር። የቃል ኪዳኑ ፍጻሜ፥ ሁል ጊዜም ቃሉን በሚጠብቀው በእግዚአብሔር ተአማኒነት ላይ የተመሠረተ ነበር።

51ኛ ጥያቄ፤ ሮሜ 8፡31-39 እና ዕብ. 7፡20-25 አንብብ። ሀ) ለእኛ የተሰጡን አንዳንድ የተስፋ ቃሎች ምንድናቸው?

ለ) እግዚአብሔር ለአብራም ከሰጠው የተስፋ ቃሎችና ፍጻሜያቸው፥ ለእኛ ስለተሰጠን የተስፋ ቃሎች ፍጻሜ ምን እንማራለን?

በአስቸጋሪ ሁኔታዎች መካከል፥ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች እውነተኛነት መጠራጠሩ ቀላል ይሆናል። ዳሩ ግን በእምነት የሚራመድ ወንድ ወይም ሴት፥ እግዚአብሔር ሥራውን እንዲሠራ በትዕግሥት መጠበቅን መማር አለባቸው። እግዚአብሔር በአመዛኙ ከእኛ የጊዜ ሰሌዳ አኳያ አይሠራም። አይቸኩልም። ይሁንና ሁል ጊዜም እንውነተኛ በመሆኑ፥ የተስፋ ቃሎቹም ሁል ጊዜ ይፈጸማሉ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ለእርሱ ከገባቸው የተስፋ ቃሎች አብራም አብዛኛዎቹን ተፈፅመው ባያያቸው፥ ከእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ውስጥ አንድ እንኳ ሳይፈጸም እንዳልቀረ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ለመመልከት እንችላለን። ይህ አምላካችን ሥራችንን እስኪሠራልን ድረስ፥ በእምነታችን ጸንተን እንድንቆም ሊረዳን ይገባል።

አምስተኛ ቀን፡- የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት እንዲረዳህ፥ የውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ስምንታዊ የአምልኮ ጊዜ

2. ጸሎት

3. የትምህርቱ ክለሳ

4. የውይይት ጊዜ

ሀ. እግዚአብሔር አብራምን፥ አገሩን፥ ሕዝቡንና ቤተሰቡን እንዲተው ነገረው። 1) የእኛ ጥሪ ከዚህ ጋር የሚመሳሰለው ወይም የሚለየው እንዴት ነው?

2) ይህ አስቸጋሪ የሚሆነው እንዴት ነው?

3) ሉቃ. 14፡25-27፥33 ከሕይወታችን ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ተወያዩ።

ለ. 1) ከአብራም ታሪክ ውስጥ የተመለከትናቸውን የተለያዩ የእምነት መመሪያዎች ዘርዝር።

2) ከእነዚህ አንዳንዶቹ በሕይወትህ የተገለጹት እንዴት ነው? ለብዙ ክርስቲያኖች አስቸጋሪ የሚሆኑትስ የትኞቹ ናቸው?

ሐ. 1) አንድ ክርስቲያን መሪ መልካም ስም የሚያስፈልገው ለምንድነው?

2) ብዙ ክርስቲያኖች ለምን ይዋሻሉ?

3) ክርስቲያን መሪዎች ለመዋሸት የተፈተኑባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ።

4) ለመዋሸት የተፈተኑት ለምንድነው?

መ. መጥፎ ውሳኔዎች፥ ይቅርታ ካገኙ በኋላ እንኳ ለረዥም ጊዜያት፥ በክርስቲያን መሪዎች ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ የሚችሉት እንዴት ነው?

ሠ. 1) አብራምና ሎጥ በብልጽግና ላይ ከነበራቸው አመለካከት ምን እንማራለን?

2) ዕብ. 11፡8-16 አንብብ።

3) ሀብት ለክርስቲያን መሪዎች አደገኛ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?

ረ. 1) የክርስቲያን ሕይወት ጦርነት የሚመስለው እንዴት ነው?

2) ጠላቶቻችን እነማናቸው?

3) የጦር ዕቃዎቻችን ምንድናቸው?

4) ድልን የምንቀዳጀው እንዴት ነው?

5. ጸሎት

ትምህርት ሰባት

ዘፍጥረት 16-19

የመጀመሪያ ቀን ዘፍጥረት 16

እስካሁን የእግዚአብሔር ወዳጅና የእምነት ሰው የሆነውን የአብራምን ሕይወት እያጠናን ነበር። ባለፈው ሳምንት፥ እግዚአብሔር ለአብራም ልጅና የከነዓን ምድር እንደሚሰጠው የተስፋ ቃል በመግባት፥ እንዴት ዘላለማዊ ቃል ኪዳን እንዳደረገ ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ «አብራም እግዚአብሔርን አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» ይላል። የአብራም ሕይወት ባመዛኙ የእኛ ዓይነት ነው። ታላላቅ የእምነት እርምጃዎች የሚደረጉባቸው ጊዜያት አሉ፤ እንዲሁም እምነታችን ጠውልጎ በእራሳችን ፍላጎት የምንመላለስባቸው ጊዜያት አሉ። ዛሬም አብራምና ሦራ በእምነት ለመጓዝ ባለመቻላቸው፥ በውጤቱ ሕይወታቸው በሙሉ፥ የልጆቻቸው ሕይወት፥ እና ዓለሙ በሙሉ የተጎዳበትን ሌላ ምሳሌ እናያለን።

1ኛ ጥያቄ፤ ሀ) በሕይወትህ ያልተለመደ ነገር እንድታደርግ እግዚአብሔር የረዳህን ጊዜ ተናገር።

ለ) በሕይወትህ እምነትህ የደከመበትን ጊዜ ተናገር።

2ኛ ጥያቄ፤ ዘፍ. 16-19 አንብብ። ሀ) በአብራም ሕይወት ውስጥ የእምነትን መታጣት የሚጠቁሙ ክስተቶችን ዘርዝር።